# አዲስ ዘመን

ኢናድ

ዓርብ

81ኛ ዓመት ቁጥር 350 ነሐሴ 20 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72

ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18

ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ


## ትሕነግ ለትግራይ ሕዝብ ሰላምና መረጋጋት ግድ የሌለው ቡድን መሆኑን በተደጋጋሚ ያስመሰከረ ስብስብ ነው

**ፍቃዱ ዴሬሳ**



አቶ ሌንጮ ለታ

አዲስ አበባ፡- ትሕነግ መንግሥት ያስቀመጠውን የሰላም አማራጭ ወደ ጎን ትቶ ጦርነት መክፈቱ ለትግራይ ሕዝብ ሰላምና መረጋጋት ግድ የሌለው ቡድን መሆኑን በተደጋጋሚ ያስመሰከረ ስብስብ ነው ሲሉ ፖለቲከኛው አቶ ሌንጮ ለታ ተናገሩ።

አቶ ሌንጮ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት አስተያየት፤ መንግሥት በተደጋጋሚ ለሰላም ቅድሚያ ሰጥቶ እጁን ቢዘረጋም አሸባሪው ትህነግ የሰላም አማራጭን ወደ ጎን በመተው ወደ ጦርነት መግባቱ በትግራይ ሕዝብ ላይ የሚደርሰው ሰቆቃ የከፋና አሳዛኝ ይሆናል።

ቡድኑ በተለያየ ወቅት ለሕዝቡ እንደሚታገል፣ ለሕዝቡ ሲልም መስዋዕትነትና ዋጋ እየከፈለ እንደሚገኝ ሲገልጽ የሚሰማ ስብስብ ቢሆንም የትግራይ ሕዝብ ግን ጉዳዩ እንዳልሆነ በተደጋጋሚ አሳይቷል ብለዋል።

ከዚህ ቀደም ከትሕነግ ቡድን ጋር ለበርካታ ጊዜያት ድርድር ያደረጉ መሆናቸውን ያወሱት አቶ ሌንጮ፣ ችግሮችን በድርድር ከመቅረፍ ይልቅ በጦርነትና በኃይል ለመፍታት የሚሞክር ኃይልና ስብስብ መሆኑን ገልጸዋል።

የትግራይ ሕዝብ የቡድኑን ተግባር በተገቢው በማጤንና በመለየት ቡድኑ በለኮሰው ጦርነቱ ውስጥ ተሳታፊና ተባባሪ መሆን እንደሌለበት አመልክተው፤ የሽብር ቡድኑ የጀመረው ጥቃት ወደ ተባባሰ ጦርነትና ቀውስ እንዳያመራም በሚችለው ሁሉ መታገል እንዳለበትም


ትሕነግ ለትግራይ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


## ሕወሓት በሕዝብ ስም የገባን ነዳጅና የሰብዓዊ ድጋፍ ለወታደራዊ ዓላማ እያዋለ መሆኑን መንግሥት አስታወቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው የሕወሓት ቡድን በትግራይ ሕዝብ ስም የገባን ነዳጅና የሰብዓዊ ድጋፍ እየዘረፈና ለወታደራዊ ዓላማ ማዋሉን ቀጥሏል ሲል የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስታወቀ።

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ትናንትና ባወጣው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ የሽብር ቡድኑ ለሰብዓዊ ዕርዳታ የሚገባን ነዳጅና የምግብ ድጋፍ ለጦርነት ዓላማ ሲዘርፍና ሲጠቀም የመቆየቱን ሃቅ ለመላው ዓለም በግልጽ ያሳየ ነው።

ለትግራይ ሕዝብ አንገብጋቢ የሆኑትን የምግብና የግብርና ግብዓቶች ለማከፋፈል ወደ ክልሉ በገባው ነዳጅ ላይ ዝርፊያ መፈጸሙ የሽብር ቡድኑ በትግራይ ሕዝብ የሚነግድ ኢሰብዓዊ መሆኑን በተጨባጭ አረጋግጧል ብሏል መግለጫው።

በተጨማሪም የቡድን ዝርፊያ ግልጽ የጦር ወንጀልና ዓለምአቀፍ የሰብዓዊነት ሕግጋቶችንም የጣሰ ድርጊት ነው ሲል አገልግሎቱ አስታውቋል።

የሽብር ቡድኑ የተፈጸመው የሰብዓዊ እርዳታ ዝርፊያ በዓለም የምግብ ፕሮግራምና በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብዓዊ እርዳታ ማስተባበሪያ ጉዳዮች ቢሮም መረጋገጡን ያስታወሰው መግለጫው፤ ቡድኑ


ሕወሓት በሕዝብ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት

FDRE Government Communication Service



ዶክተር ይልቃል ከፋለ

## በአንድነት በመቆም ልማቱንም በአሸባሪው ሕወሓት የተከፈተውን ጦርነት በአሸናፊነት መወጣት ይቻላል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በአንድነት ቆመን ልማቱንም በአሸባሪው ሕወሓት የተከፈተብንን ጦርነትም በአሸናፊነት እንወጣለን ሲሉ የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ ገለጹ፡፡

ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ የወልድያ ከተማ ከፈርጅ አንድ ወደ ሪጂዮፖሊታን የደረጃ ሽግግር የእውቅና መርሃ ግብር ትናንት በወልድያ ከተማ ሲካሄድ እንደገለጹት፤ የጀመርነው የልማት እና የእድገት ጉዞ በተከፈተብን ጦርነት አይደናቀፍም፤ የገጠመንን ጦርነት በትግላችን፤ ድህነታችንን ደግሞ በልማት እናሸንፋለን፡፡


በአንድነት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




## “አሸባሪው ሕወሓት በጦርነት ያልተሳተፈ ከጥቅም ይገለላል ማለቱ የተስፋ መቁረጡ ምልክት ነው”

- አቶ ሃይለ ገብረሚካኤል


ገጽ 4



አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ

ADAMA STEEL FACTORY

ሚስማር ከ3 ቁጥር -15 ቁጥር

የበረንዳ ታይልስ ኤጋ መደበኛ ኮልሞ

0940 505050/0940 606060/0940 909090/0940 808080/0920 656565

UNIC ETHIOPIA

ሕብረት ኢንሹራንስ አማ

THE UNITED INSURANCE COMPANY SC

Tomorrows Company Today‘

+251 111 26 34 34

united.insurance@unic-ethiopia.com

ለ ሁሉም የመድን ፍላጎትዎ

ለህይወት

ህጋዊ ግዴታዎ

# ለስራ አጥ ወጣቶች የስራ ላይ ልምምድ የሚሰጡ አንድ ሺህ 505 ተቋማት መለየታቸውን ቢሮው አስታወቀ

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- ለስራ ፈላጊ ወጣቶች የስራ ላይ ልምምድ የሚሰጡ አንድ ሺህ 505 ተቋማት መለየታቸውን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥራ ኢንተርፕራይዝ እና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ እና የሥራ ኢንተርፕራ ይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ ጃንጥራር አባይ ትናንትና በሰጡት መግለጫ እንዳስታወቁት፤ በአዲስ አበባ ለሚገኙ 10 ሺህ 500 ሥራ አጥ ወጣቶች የስራ ላይ ልምምድ መስጠት የሚችሉ አንድ ሺህ 505 ተቋማት ተለይተዋል።

ቢሮው "ብቃት የወጣቶች የተግባር ላይ ልምምድ" የተሰኘ ፕሮግራም በመቅረጽ ከዓለም ባንክ ጋር በትብብር በሶስት ዓመታት ውስጥ ለ49 ሺህ ስራ አጥ ወጣቶች የስራ ላይ ልምምድ እንዲያገኙ እየሰራ መሆኑን አቶ ጃንጥራር ገልጸዋል።

በመጀመሪያው ዙር የስራ ላይ ልምምዱን ለወጣቶች ለመስጠት ፈቃደኛ የሆኑ የተለያዩ ተቋማትም በማምረቻ፣ በሆቴልና ቱሪዝም፣ በአገልግሎትና በተለያዩ ዘርፎች ላይ የሚገኙ ድርጅቶች መሆናቸውን ጠቁመዋል።

ወጣቶቹን በየተቋማቱ ለስድስት ወራት ያህል እየሰሩ የሕይወት ክህሎቶችን፣ የኮምፒውተርና አጠቃላይ የስራ ላይ ክህሎት እንዲያገኙ ይደረጋል ሲሉ ተናግረዋል።

ፕሮግራሙ ላይ የሚካፈሉ ወጣቶች የኪስ ገንዘብ ተመድቦላቸው ለግማሽ ዓመት እንዲሰሩ ይደረጋል ያሉት አቶ ጃንጥራር፤ ዕድሜያቸው ከ18 እስከ 25 ያሉ የከተማዋ ወጣቶች ለዚሁ ፕሮጀክት ተመዝግበው ሥልጠና እያገኙ መሆኑን ጠቁመዋል።

ፕሮጀክቱ ከዓለም ባንክ በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ እንደሚካሄድ የገለጹት ኃላፊው፤ እስካሁን ከ27 ሺህ በላይ ሥራ ፈላጊ ወጣቶች መመዝገባቸውን ጠቁመዋል።

የስራ ላይ ልምምድ ዕድሉን ከሚያገኙት የመጀመሪያ ዙር ወጣቶች መካከል 60 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች መሆናቸውንም የቢሮው ኃላፊ ተናግረዋል።

በሁለተኛው ዙር የስራ ላይ ልምምድ ዕድሉን የሚያገኙ ወጣቶች 12 ሺህ መሆናቸውን ጠቁመው ፤



አቶ ጃንጥራር አባይ

ከሁለት ወራት በኋላ ወደ ስራ እንደሚገቡና ፤ ለዚህም የተቋማት ልየታ ስራ እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

በስራ ላይ ልምምዱ የሚካፈሉ ወጣቶች እንደየብቃታቸውና እንደየተቋማቱ ሁኔታ ከስድስት ወራት በኋላም ተቀጥረው የሚሰሩበት ዕድል ሊኖር እንደሚችል የገለጹት አቶ ጃንጥራር፤ ወጣቶቹ ለዚህ የሚረዳቸውን አስፈላጊ ዝግጅት እንዲያደርጉ የሚያግዝ ሥልጠና እየተሰጠ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

የወጣቶች የስራ ላይ ልምምድ ፕሮጀክትን በአዲስ አበባ ሁሉም ክፍለከተሞች በሚገኙ 36 ወረዳዎች እንደሚተገበር ምክትል ከንቲባና የቢሮው ኃላፊ አቶ ጃንጥራር አስታውቀዋል።

በአጠቃላይ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ የሚደረገው የስራ ላይ ልምምድ ፕሮጀክት በ11 ከተሞች ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን፤ አዲስ አበባ ትልቁን ድርሻ በመያዝ 49 ሺህ ወጣቶችን ታሳትፋለች ሲሉ ገልጸዋል።

የስራ ላይ ልምምድ ፕሮጀክቱ በ11 ከተሞች የሚካሄድ ሲሆን በአጠቃላይ 70 ሺህ ወጣቶችን ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ተገልጿል።

በአዲስ አበባ ከተማ ካለው የስራ አጥ ቁጥር ውስጥ 82 በመቶ የሚሆነው ከ12ኛ ክፍል በታች የትምህርት ዝግጅት ያላቸው መሆናቸውን ቢሮው አስታውቋል።

# በ 7 ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር የተገነባው የመነጽር ማምረቻ ማእከል ሥራ ጀመረ

**አስናቀ ፀጋዬ**

አዲስ አበባ፡- በአለርት ጠቅላላ ሆስፒታል ውስጥ በ 7 ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር ወጪ የተገነባው የመነጽር ማምረቻ፣ የሬቲና ጨረር ህክምናና የአይን ሬቲና ደረጃ መመርመሪያ ማእከል ስራ ጀመረ፡፡

በአለርት ሆስፒታል የአይን ህክምና ክፍል ሃላፊ ዶክተር ሰለሞን ቡሳ በተለይም ለአዲስ ዘመን እንደገለጹት፤ ከዚህ ቀደም አዋቂዎችም ሆኑ ሕፃናት የእይታ ችግር እያለባቸው መነጽር ሲታዘዝላቸው መነጽሩን የመግዛት አቅም አይኖራቸውም፡፡ በሆስፒታሉ ውስጥ የእይታ ችግር ያለባቸው ሰዎች መነጽር ሲታዘዝላቸው እዛው ተሰርቶ እንዲሰጣቸው የሚያስችል የመነጽር ማምረቻ ማእከል በመከፈቱ ለመነጽር ግዢ የሚወጡትን ወጪና እንግልት የሚቀንስ ነው፡፡

ገንዘብ የሌላቸውና የጤና መድህን አገልግሎት ተጠቃሚ ያልሆኑት ደግሞ መነጽሩ በነፃ እንደሚሰራላቸውም ገልጸዋል፡፡

ይህ የመነጽር ማምረቻ ማእከል ሲሰራ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በስኳር በሽታ ምክንያት የሚከሰተውን የሬቲና መድማት፣ ውሃ መቋጠርና የመሳሰሉትን ነገሮችን በመመርመር የጨረር ህክምና ለመስጠት የሚያስችል ክፍል መዘጋጀቱንም ሃላፊው ጠቅሰዋል፡፡

ለዚሁ ምርመራና ህክምና አስፈላጊ የሆኑ መሳሪያዎች መሟላታቸውንም አስታውቀዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የአይን ዋና መመልከቻ ሬቲና ደረጃውን የሚመረምርና የሚያሳይ ክፍል አብሮ መኖሩንም ጠቅሰዋል፡፡

ማእከሉን ገንብቶ ለማጠናቀቅ አምስት ወራት እንደፈጀ የጠቀሱት ሃላፊው፤ ጠቅላላ ግንባታውን ለማከናወን 7 ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር ወጪ መደረጉን አመልክተዋል፡፡ ይህንንም ጠቅላላ ወጪ የሸፈነው ሲ ቢ ኤም የተሰኘው የጀርመን ግብረሰናይ ድርጅት መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

ማእከሉ በቀን 20 የሚሆኑ የሬቲና ምርመራና ጨረር ህክምና የሚፈልጉ ሰዎችን የማስተናገድ አቅም እንዳለውና በአማካይ በቀን 30 ለሚሆኑ የመነጽር ምርመራ ፈላጊዎች አገልግሎት የመስጠት አቅም




እንዳለውም ሃላፊው ተናግረዋል፡፡

የመነጽር ማምረቻ ማእከሉ የሆስፒታሉ የአይን ህክምና ክፍል አንዱ ማስፋፊያ መሆኑን አመልክተው፤ ህክምና ክፍሉ ስምንት የአይን ስፔሻሊስትና አራት የመነጽር ባለሙያዎችን አሟልቶ የአይን ህክምና አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡



# መስሪያ ቤቶች በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚፈጽሙት ክፍያ በሳምንት 5 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር ደረሰ

አዲስ አበባ፡- የፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መስሪያ ቤቶች በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚፈጽሙት ክፍያ በሳምንት 5 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር መድረሱን ገንዘብ ሚኒስቴር አስታወቀ።

የገንዘብ ሚኒስቴር ከፌዴራል መንግሥት ባለበጀት መስሪያ ቤቶች ጋር በኤሌክትሮኒክ ክፍያ አፈጻጸም ላይ ተወያይቷል።

በኢንተርኔት ባንኪንግ የተከናወኑ ክፍያዎች በጥቅምት 2014 ዓ.ም ሲጀመር በሳምንት 900 የነበሩት ክፍያዎች በአሁኑ ወቅት በሳምንት ከ 12 ሺህ በላይ ክፍያዎች በኤሌክትሮኒክ ክፍያ ስልት እየተፈጸመ መሆኑን ተገልጿል፡፡

በውይይቱ ከጥቂት መስሪያ ቤቶች በስተቀር ሁሉም የፌዴራል ባለበጀት መ/ቤቶች የኤሌክትሮኒክ ክፍያ ስርዓቱን በስራ ላይ እንዳዋሉና አንዳንድ መስሪያ ቤቶች ክፍያዎችን ሙሉ በሙሉ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ማከናወን ደረጃ ላይ መድረሳቸው የተገለጸ ሲሆን፣ በርካታ መስሪያ ቤቶች 50 በመቶ ክፍያዎችን በኤሌክትሮኒክ ክፍያ በማከናወን ላይ መሆናቸው ታውቋል፡፡

የፌደራል መንግሽት መስሪያ ቤቶች የኤሌክትሮኒክ ክፍያውን መጠቀም ከጀመሩ በኋላ ጥቅሙን እና አስተማማኝነቱን በመረዳት ክፍያዎቻቸውን በቼክ፣ በጥሬ ገንዘብ፣ እና በደብዳቤ ከማከናወን ይልቅ ወደ ኤሌክትሮኒክ ክፍያዎች ዘዴ እያዘነበሉ መሆናቸውም ተገልጿል፡፡

በሌላ በኩል ወደ ሥርዓቱ አለመግባት፣ የሂሣብ ሪፖርትና የመንግሥት ሌተር ኦፍ ክሬዲት (L/C) የአፈጻጸም ሪፖርት በወቅቱ አለማቅረብ፣ ለመንግሥት ገቢ መደረግ ያለበትን ገንዘብ በወቅቱ ያለማስገባት፣ ዓመታዊ የጥሬ ገንዘብ ዕቅድን በአግባቡ ያለማቀድና ከተደገፈው የጥሬ ገንዘብ ዕቅድ በላይ የመጠየቅ ችግሮች መኖራቸውንም ተስተውሏል፡፡

በአጠቃላይ የመንግሥት የደመወዝ፣ የግዢና የአገልግሎት ክፍያዎችን በኤሌክትሮኒክ ክፍያ መፈጸም ቀልጣፋ፤ ግልፅና ወጪ ቆጣቢ አገልግሎት ከመስጠቱም ባሻገር የሀገሪቱን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሚያሻሽል መሆኑ የሚኒስቴር መስሪያቤቱ መረጃ ያመለክታል።

የፌዴራል መንግሥት የኤሌክትሮኒክ ክፍያ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 71/2013 አምና የወጣ ሲሆን ከ2014 በጀት ዓመት ጥቅምት ወር ጀምሮ የክፍያ ሥርዓቱ ትግበራ መጀመሩ ይታወሳል፡፡



## ‹‹አሸባሪው ሕወሓት የፈጸመው ነዳጅ ዘረፋ በመሪነት ዘመኑ ጭምር አገርን የመዘበረ የተራ ወሮበላዎች ስብስብ እንደሆነ ያሳየ ነው››

\- አቶ ሙሉብርሃን ኃይሌ
የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው ሕወሓት መቀሌ በሚገኘው የዓለም የምግብ ድርጅት መጋዘን ውስጥ የነበረን 570 ሺህ ሊትር ነዳጅ መዝረፉ በመሪነት ዘመኑ አገርን የመዘበረ የተራ ወሮበላዎች ስብስብ እንደሆነ ያሳየ መሆኑን የትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ትዴፓ) የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ሙሉብርሃን ኃይሌ ገለጹ። ቡድኑ ችግሮችን በሰላም መፍታት የሚያስችል ሞራል ስለሌለው የለመደውን የቁማር ጦርነት ጀምሯል።

አቶ ሙሉብርሃን ኃይሌ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አሸባሪው ሕወሓት በትግራይ ሕዝብ ስም 50 ዓመት ሙሉ የነገደ የወንበዴዎች ድርጅት ነው። አሸባሪው ሕወሓት መቀሌ በሚገኘው የዓለም የምግብ ድርጅት መጋዘን ውስጥ የነበረን 570 ሺህ ሊትር ነዳጅ መዝረፉ ሰሞኑን የሰብዓዊ ዕርዳታ ለትግራይ ሕዝብ ለማድረስ ነዳጅ የለም በማለት ሲሰራጭ የነበረውን መረጃ ሀሰት መሆኑን ራሱ የመሰከረበት ነው። ይህ ተግባሩ አሸባሪው ቡድኑ ለትግራይ ሕዝብ ደንታ እንደሌለውና የሌቦች ስብስብ መሆኑን ያሳየ ነው።

እንደ አቶ ሙሉብርሃን ገለጻ፤ አሸባሪው ቡድን ነዳጅ መዝረፍ ብቻ አይደለም በእርዳታ እህል ከሚተዳደረው የትግራይ ሕዝብ ከ15 ኪሎ ሶስቱን ኪሎ የሚሰርቅ አሳፋሪ ነው። በትግራይ ሕዝብ ስም 50 ዓመት ሙሉ የነገደ ነው። ቡድኑ ለትግራይ ሕዝብ ተቆርቋሪ፣ ነጻ አውጭ፣ ብቸኛ ወኪልና ጠባቂ ነኝ ቢልም በተግባር ሲታይ ግን በትግራይ ሕዝብ ስም እየነገደና እየሸቀጠ የሚኖር ነው።

ቡድኑ ለትግራይ ሕዝብ የሚላከውን የምግብና መድሃኒት ዕርዳታ ሳይቀር እንደሚዘርፍ አውስተው፤ ለገባበት የፖለቲካ ቁማር ሕዝቡን አስይዞ የሚጫወትና በትግራይ ሕዝብ ስም የተደራጀ ግን ባህሪው ለትግራይ ሕዝብ ሥነ ልቦና የማይመጥን የተራ ወሮበላዎች ስብስብ ነው ብለዋል።

አሸባሪው ሕወሓት ለትግራይ ሕዝብ ሰብዓዊ እርዳታ ማጓጓዝ እንዲሆን መቀሌ በሚገኘው የዓለም የምግብ ድርጅት መጋዘን ውስጥ የነበረን 570 ሺህ ሊትር ነዳጅ መዝረፉ ለትግራይ ሕዝብ ጠላት መሆኑን ተጨማሪ ማረጋገጫ መሆኑን አመልክተው፤ በድርጊቱም የአሸባሪው ሕወሓት ስብስቦች ትግራይ ውስጥ የበቀሉ ነገር ግን የትግራይ ሕዝብ ሥነልቦና የሌላቸውና ሕዝቡን የማይወክሉ ወንጀለኞች መሆናቸውን በተጨባጭ ያሳዩበት መሆኑንም ገልጸዋል።

የሕወሓት ስብስብ ለትግራይ ሕዝብ የተላከን ዕርዳታና ነዳጅ ከመስረቁም በተጨማሪም አካሄዳችሁ ትክክል አይደለም ብሎ የሚሞግታቸውና እውነተኛ ኢትዮጵያዊ የሆኑ የትግራይ ልጆችን እየበላ የመጣ የጥፋት ስብስብ መሆኑን ገልጸዋል።

ቡድኑ ያለ ጦርነት ዝም ብሎ ሊቀመጥ አይችልም ያሉት አቶ ሙሉብርሃን፤ በጦርነት ለትግራይ ሕዝብ ያመጣው አንድም ነገር የለም። አሁን በሰላምም መኖር የማይችልበት ደረጃ ላይ በመድረሱና ብዙ ወንጀሎች የፈጸመ በመሆኑ ሕዝቡ ጥያቄ ያነሳብኛል ብሎ በመፍራት የውሸት ፕሮፓጋንዳና ትርክቶችን እንደ አዲስ እየቀሰቀሰ የትግራይን ወጣት ወደ ጦርነት እየማገደ መሆኑን ተናግረዋል።

የትግራይ ሕዝብ ችግር ውስጥ እንዲገባ ያደረገውና ጦርነት የጀመረውም ራሱ አሸባሪው ቡድን በመሆኑ ዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ ሊያወግዘውና ሊኮንነው ይገባል ሲሉ ገልጸዋል።

ቡድኑ በድርድር ችግሮችን በሰላም መፍታት የሚያስችል ሞራል የለውም ያሉት አቶ ሙሉብርሃን፤ የትግራይ ሕዝብ ትርጉም በሌለው ጦርነት ከመሳተፍ ይልቅ አሸባሪውን ቡድን ሊያወግዝና ሊታገል እንደሚገባ ጥሪ አቅርበዋል።

# የትግራይ ሕዝብ የጥፋት ኃይሉ የሰላም አማራጭን እንዲቀበል ጫና ማድረግ እንዳለበት ተገለጸ

**ዘላለም ግዛው**



አዲስ አበባ፡- የትግራይ ሕዝብ ከጥፋት ኃይሉ ራሱን በመነጠል አሸባሪው የሕወሓት ቡድን መንግሥት የዘረጋውን የሠላም አማራጭ እንዲቀበል ጫና ማድረግ እንዳለበት የአማራ ክልል የብልጽግና ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ግርማ የሺጥላ ጥሪ አቀረቡ።

አቶ ግርማ የደብረ ብርሃን ከተማ አስተዳደር በህልውና ዘመቻ ለተሳተፉና ከፍተኛ ዋጋና መስዋዕትነት ለከፈሉ የከተማዋ ነዋሪዎች ትናንት የምስጋናና የእውቅና መርሃ ግብር ባካሄደበት መርሃ ግብር እንደገለጹት፤ ችግሮች የሚፈቱት በሰላም እንጂ በጦርነት አይደለም፡፡ የትግራይ ሕዝብም ከጥፋት ኃይሉ በመነጠል ከመንግሥት የተዘረጋውን የሠላም አማራጭ ቡድኑ እንዲቀበል ጫና ማድረግ አለበት።

ሃይል፣ ጉልበትና ጡንቻ የችግር መፍቻ አይደለም ያሉት አቶ ግርማ፤ አሁንም ችግሮች የሚፈቱት በሰላም አማራጭ ነው ብለዋል። ሆኖም ትህነግ ችግሩን በሰላማዊ አማራጭ ከመፍታት ይልቅ ለሶስተኛ ጊዜ የዳግም ወረራ መንቀሳቀሱን ነው የተናገሩት። አይደለም፡፡ የትግራይ ሕዝብም ከጥፋት ኃይሉ ራሱን በማግለል ከመንግሥት የተዘረጋውን የሠላም አማራጭ ቡድኑ እንዲቀበል ጫና መፍጠር እንደሚኖርበት ተናግረዋል፡፡

በጠላት ላይ ድል በማስመዝገብ ሂደት የሕዝቡ ሚና ከፍተኛ እንደነበር አቶ ግርማ አንስተዋል። ሕዝቡ ሥነምግባር በተሞላበት ሁኔታ ለክተት አዋጁ የሰጠው ምላሽ በታሪክ የተመዘገበ መሆኑንም አመልክተዋል።

ለሠላም የማይናወጥ አቋም አለን፣ የሌላውን ሰላም፣ ጥቅምና ፍላጎት ለመንጠቅ የፈጸምነው፣ የምንፈጽመውም ጀግንነት የለም፤ አይኖርም ብለዋል።

ለሠላም ካለን ፍላጎት ትክክለኛና ፍትሃዊ ጀግንነት እንከፍላለን። በዳግም ወረራው በመዘናጋት ለጸጥታ ችግር ላለመጋለጥ መጠንቀቅ ይገባል ነው ያሉት።

ወራሪን የመከላከል ሥራው በቅንጅትና በምሉዕነት መከናወን እንደሚኖርበትም አሳስበዋል። ደጀኑ ጥልቅ፣ የማይፈታና ጠንካራ መሆን እንደሚገባውም አሳስበዋል።

የከተማው የሠላምና የሕዝብ ደህንነት መምሪያ ሃላፊ አቶ አበራ መኮንን፤ እብሪተኛውና አገር ከፋፋዩ የትህነግ ቡድን የፈጸመውን ወረራ ተከትሎ በክተት አዋጅ ለተገኘው ድል እውቅና መስጠትና ማመስገን ከሞራልም በላይ ለተጨማሪ ድል ማዘጋጀት ነው ብለዋል።

ሕዝቡና የጸጥታ ሃይሉ በነበረው ሁለንተናዊ ተሳትፎ ለተገኘው ድል በይፋ ማመስገን ለቀጣይ ተልእኮ ማዘጋጀት ጭምር መሆኑንም ተናግረዋል። የሕይወት መስዋእትነት ተከፍሎ ለተገኘው ድልም አመስግነዋል።

የትህነግ ተላላኪና ወራሪ ሃይል ከኢትዮጵያ ታሪካዊ ጠላቶች ጋር በመቀናጀት ለዳግም ወረራ የተንቀሳቀሰበት ወቅት እንደመሆኑ አገርና ሕዝብን የማዳን ተግባርን በብቃት እንዲወጡም አደራ ብለዋል።

ሕዝቡ ብልሹ አሰራሮችን እንዲያጋልጡና እንዲታገሉ፣ የኢንዱስትሪ ሰላምን በማስጠበቅ ሃላፊነታቸውን እንዲወጡም አሳስበዋል። የሃይማኖት አባቶችና የአገር ሽማግሌዎች ወጣቱ ስራ ፈጣሪና ግብረገብ እንዲሆን፣ ታሪኩን እንዲያውቅና እንዲጠብቅ ሃላፊነታቸውን እንዲወጡም ጠይቀዋል።

ከተማዋ ወደ ኋላ እንድትቀር ተደርጎ ነበር፣ አሁን የደብረ ብርሃን ሪጂዮ ፖሊታን ከተማ የሥልጣኔ ከተማነቷን፣ ታሪካዊና ጥንታዊነቷን አስጠብቃ መቀጠል መቻሏን ጠቁመዋል።

የከተማው ተቀዳሚ ምክትል ከንቲባ አቶ ካሳሁን አምቢአለ በበኩላቸው፤ አባቶች አገርን ከጠላት ጠብቀው ከነሙሉ ክብርና ዝናዋ ማስረከባቸውን አስታውሰዋል። የጀግንነት ታሪክ የኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን የጥቁሮች ተምሳሌት አድርጎናል ነው ያሉት።

ኢትዮጵያ በበርካታ ፈተናዎች ላይ ትገኛለች ያሉት አቶ ካሳሁን፤ በአገርና በአንድነት ሳንደራደር የተቀበልነውን አደራ ማስጠበቅ እንደሚገባም አመልክተዋል። የትህነግ ወራሪ ሃይልን በማሳፈር አኩሪ ድል መመዝገቡንም ተናግረዋል። የጸጥታ ሃይሎችና የሰሜን ሸዋና የደብረ ብርሃን ከተማ ሕዝብ ክብር ይገባዋል ሲሉም ገልጸዋል።

ከተማ አስተዳደሩ በሕልውና ዘመቻው ተሳትፎ በማድረግ የቆሰሉ፣ የዘመቱ እና የተሰዉ የከተማው ነዋሪዎች እውቅና እና ምስጋና ይገባቸዋል፣ ውለታቸው በታሪክ ተመዝግቦ እንደሚቀመጥም ነው የገለጸው።

ሕይወታቸውን ሰውተው አገርን ከመደፈር ከመፍረስ የታደጉ አሁንም ጠላትን ተዋግተው ኢትዮጵያን ለማሻገር እየተዋደቁ ለሚገኙ ክብር ይገባቸዋል ተብሏል።

# የላዳ ታክሲ ቅያሪ ተሽከርካሪዎች ድሬዳዋ ላይ መገጣጠም መጀመራቸው ተገለጸ

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- ከቀረጥ ነፃ የገቡ የላዳ ታክሲዎች ቅያሬ ተሽከርካሬዎች ድሬዳዋ ከተማ ላይ እየተገጣጠሙ መሆኑን የፋብሪካው አመራር ገለጸ።

የላዳ ተሽከርካሪ ማሕበራት ለቅያሬ ተሽከርካ ሪዎቻቸውን መገጣጠሚያ የሚሆኑ ግብዓቶችን ከቀረጥ ነፃ እንዲያስገቡ የሚፈቅደው መመሪያ ከሐምሌ ወር ጀምሮ ወደ ትግበራ መግባቱን የገንዘብ ሚኒስቴር አስታውቋል።

የኤል አውቶ ኢንጂነሪንግና ትሬዲንግ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ በቀለ አበበ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በመጀመሪያው ዙር የሚገጣጠሙ የላዳ ቅያሬ ተሽከርካሪዎች ግብዓቶች ወደ ድሬዳዋ ኢንዱስትሪ ፓርክ ገብተው የመገጣጠም ሥራው በወሩ አጋማሽ ላይ በተሳካ ሁኔታ ተጀምሯል።

በአጠቃላይ 10 ሺህ 500 መቶ የላዳ ቅያሬ ተሽከርካሪዎችን ለመገጣጠም ከአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድርና ከአሽከርካሪ ማሕበራት ጋር ስምምነት መደረጉን ያስታወሱት አቶ በቀለ፤ የመገጣጠም ስራውን በፍጥነት በማከናወን ለባለቤቶቹ ለማስረከብ ጥረት እንደሚደረግ ተናግረዋል።

እንደ ሥራ አስኪያጁ ገለጻ፤ የተሽከርካሪዎቹን መገጣጠም ስራ ለማቀላጠፍ የሚረዱ ሁለት ፋብሪካዎች ዱከምና ድሬዳዋ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ይገኛሉ። የዱከሙ መገጣጠሚያ ፋብሪካም በቀጣይ ሳምንት መጀመሪያ ቀናት የላዳ ተሽከርካሪዎችን የመገጣጠም ስራ ይጀምራል።

ሁለቱ ፋብሪካዎች በአጠቃላይ በቀን 52 ተሽከርካሪ የመገጣጠም አቅም አላቸው ያሉት አቶ በቀለ፤ የመገጣጠሚያ ግብዓቶችና የጉምሩክ እንዲሁም የተለያዩ ተያያዥ ጉዳዮችን ታሳቢ በማድረግ የላዳ ቅያሬ ተሽከርካሪዎቹን አንድ ዓመት ባነሰ ጊዜ ውስጥ ለማጠናቀቅ ጥረት ይደረጋል ሲሉ አስረድተዋል።

አብዛኛዎቹ የላዳ ቅያሬ ተሽከርካሪዎች ባለ ሰባት ወንበር ያላቸው ተሽከርካሪዎች መሆናቸውን ገልጸው፤ የተወሰኑት ባለ አምስት ወንበር ሲሆኑ፤ ተሽከርካሪዎቹም አንድ ሺህ ሲሲ ጉልበት ያላቸው በመሆናቸው ለነዳጅ ቁጠባም አዋጭ ናቸው ብለዋል።

የፋይናንስ አቅርቦትን በተመለከተ ለላዳ ቅያሬ ተሽከርካሪዎቹን ለመረከብ የላዳ አሽከርካሪዎች 20 በመቶውን ክፍያ ማዘጋጀታቸውን የገለጹት አቶ በቀለ፤ ቀሪው ክፍያ በባንክ ብድር የሚሸፈን መሆኑንና የመንግሥትም ድጋፍ የታከለበት ፕሮጀክት መሆኑን ተናግረዋል።

ለባንክ ብድርም የተለያዩ የመንግሥትና የግል ባንኮች አቅርቦት እንደሚያደርጉ አስታውቀዋል።

አሁን ላይ የቅያሬ ተሽከርካሪዎቹ ግብዓቶች ከቀረጥ ነፃ ለማስገባት የወጣው መመሪያ አስፈላጊው የሕግ ዝግጅት ተደርጎበት ተግባራዊ መደረጉን አስታውሰው፤ ድርጅቱ ያስገባቸውና ለወራት በጉምሩክ መጋዘን ተቀምጠው የነበሩ ተሽከርካሪዎች መገጣጠሚያ ግብዓቶችን ከቀረጥ ነጻ በሆነ መንገድ ማውጣት ተችሏል ብለዋል።

ግብዓቶቹንም በቀጥታ ወደ ፋብሪካ በመውሰድ የላዳ ቅያሬዎቹን ተሽከርካሪዎች ወደመገጣጠሙ መግባቱንና፤ በቀጣይም የቀረጥ ነፃ ዕድልን በመጠቀም ቀሪዎቹን ውል የተገባባቸውን ተሽከርካሪዎች ለመገጣጠም ጥረት እንደሚደረግ አስታውቀዋል።

በገንዘብ ሚኒስቴር የታክስ ፖሊሲ ዳይሬክተር አቶ ሙላይ ወልዱ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ለረጅም ዘመን ሕብረተሰቡን ያገለገሉ የላዳ ተሽከርካሪዎች በማርጀታቸው ምክንያት ዘመናዊ ተሽከርካሪዎችን እንዲጠቀሙ የሚረዳ አሰራር መንግሥት ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል።

በዚህ መሰረት ከባንክ ብድር ጋር በማመቻቸት በልዩ ሁኔታ ከቀረጥ ነጻ እንዲያስገቡ ለላዳ ታክሲ ማሕበራት ፍቃድ ተሰጥቷል። ከቀረጥ ነጻ ዕድሉ መመሪያ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ እንዲሆን የሚያስችል የሕግ ዝግጅት በማስፈለጉ መመሪያው ተግባራዊ ሳይሆን ለተወሰኑ ወራት ዘግይቶ መቆየቱን አስታውሰዋል።

አሁን ላይ ግን መመሪያው ተግባራዊ በመሆኑ የታክሲ ማሕበራት ከቀረጥ ነጻ እንዲያስገቡ ፈቃድ እየተሰጣቸው ይገኛል። ወደሚኒስቴሩም መጥተው የተመዘገቡ ከ200 በላይ የታክሲ ማሕበራት አሉ። አስፈላጊውን መስፈርና ዶክመንት ያሟሉ ማሕበራት አገልግሎቱን እያገኙ ነው ብለዋል።

አንድ ከቀረጥ ነጻ ፍቃድ ያገኘ የላዳ ታክሲ ማሕበር ፍቃዱን ከገጣጣሚ ፋብሪካው ጋር በማያያዝ ተሽከርካሪዎቹ እንዲገጣጠሙለት ማድረግ እንደሚችል ታውቋል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አማካኝነት ለረጅም ጊዜ አገልግሎት ሲሰጡ የቆዩ ባለ ሰማያዊ በነጭ ወይንም በተለምዶ ላዳ የተሰኙ ታክሲዎችን በአዲስ ለመቀየር የሚያስችል ስምምነት በተሽከርካሪ አቅራቢና በባለንብረቶች መካከል የተፈረመው በ2013 ዓ.ም መሆኑ የሚታወስ ነው።

ዜና

# "አሸባሪው ሕወሓት በጦርነት ያልተሳተፈ ከጥቅም ይገለላል ማለቱ የተስፋ መቁረጡ ምልክት ነው"

\- አቶ ሃይለ ገብረሚካኤል

**ሄርሞን ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- አሸባሪው የሕወሓት ቡድን በማካሂደው ጦርነት ላይ ያልተሳተፈ ማንኛውም የትግራይ ወጣት ከጥቅም ይገለላል ብሎ ማስፈራራቱ የተስፋ መቁረጡ ምልክት ነው ሲሉ በአራዳ ክፍለ ከተማ የትግራይ ብልጽግና አባል አቶ ሃይለ ገብረሚካኤል ገለጹ።

አቶ ሃይለ ገብረሚካኤል ለወጋሕታ ጋዜጣ እንደገለጹት፤ሰሞኑን የአሸባሪው ሕወሓት መሪ ዶክተር ደብረፅዮን ገብረሚካኤል በምናካሂደው ጦርነት በሚሳተፍና በማይሳተፍ መካከል የጥቅም ላይ ልዩነት እናደርጋን ያሉበት ምክንያት በጥቅም አድርገው ሕዝቡ ከጎናቸው ለማሰለፍ አስበው ነው። ይህ አካሄድ የሚያሳየው ቡድኑ የትግራይ ሕዝብ ድጋፍ እየነፈገው እንደሆነና፤ በጥቅም አስገድዶ ድጋፍ ለማግኘት የሚደረገው የተስፋ መቁረጥ መፍጨርጨር ምልክት ነው።

አሸባሪው ሕወሓት ቡድን እንደዚህ አይነት አካሄድ ከዚህ በፊትም ይጠቀምበት እንደነበር አቶ ሃይለ አውስተው፤ በተለይ ለትግራይ ሕዝብ የሚላከውን የሰብዓዊ ዕርዳታ ለደጋፊዎቹ ብቻ በማከፋፈል ልዩነት በመፍጠር የትግራይ ሕዝብ ለዕርዳታ ብሎ እሱን እንዲደግፍ ያስገድዳል። ቡድኑ ይህን የሚያደርገው የትግራይን ሕዝብ በጥቅም በማስፈራራት ከጎኑ በማስገደድ ለማሰለፍ ያለመ መሆኑን ተናግረዋል።

የትግራይን ሕዝብ በጥቅም መደለል አይቻልም ያሉት አቶ ሃይለ፤ ሕዝብ ካላመነ በጥቅም አስገድደህ ወደ ጦርነት ለመክተት ማሰብ ብዙ ርቀት የሚያስኬድ አለመሆኑን ተናግረዋል።

ይህ አካሄድ የቀደመ የአሸባሪው ሕወሓት ከፋፍሎ የመግዛት ባህሪ በመሆኑ ገሚሱ በጥቅም የተቀረው ደግሞ ከጥቅም እንዲገለል ማድረግ በትግራይ ሕዝብ ስም የመጣን ዕርዳታ ለራስ ጥቅም ማስፈጸሚያ ማድረግ ተገቢ አይደለም ሲሉ ተናግረዋል።

የሕወሓት መሪዎች እርዳታ ከማደል ጀምረው እንደዚህ ዓይነት ስራ ሲሰሩ ቆይተዋል ያሉት አቶ ሃይለ የተቸገረውን ትተው ለደጋፊዎቻቸው በብዛት ያድላሉ።

በእንደዚህ ዓይነት አካሄድ ቡድኑ ዓላማው ማሳካት አይችልም ያሉት አቶ ሃይለ፤ ሥርዓቱ አሸባሪው ሕወሓት ታጣቂዎቹ ተስፋ እየቆረጡበትና ሥርዓቱ እየፈረሰበት ስለሚገኝ፤ በጥቅም ታጣቂዎቹን ለመልመል እያደረገ ያለው ሙከራ ተስፋ መቁረጥ ላይ እንደሆነ የሚያመላክት ነው ብለዋል።



# በአንድነት በመቆም ልማቱንም በአሸባሪው...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

አሸባሪው ሕወሓት ጦርነቱን ራሱ ከፍቶ መልሶ ደግሞ ጦርነት ተከፈተብኝ በማለት ዓለም አቀፉን ማሕበረሰብ እንደለመደው ለማወናበድ እየሠራ መሆኑንም ዶክተር ይልቃል አመልክተው፤ በአሸባሪው ሕወሓት የተከፈተብንን ጦርነት አንድ ከሆንን፣ ከተደማመጥን፣ በጋራ ከቆምን እና ከተከባበርን የመጨረሻው አሸናፊዎች እኛ ነን ብለዋል።

የሽብር ቡድኑ ሁለት ጊዜ ጥቃት እና ወረራ ተከፍቶብን በሕዝባችን፣ በመከላከያ ኃይላችን እና በክልላችን የጸጥታ መዋቅር አዳሸነፍን ሁሉ አሁን የተከፈተብንን ጦርነትም በተባበረ ክንድ ማሸነፍ እንደሚቻልም ገልጸዋል።

ርእሰ መስተዳድሩ ጦርነቱ በተከፈተበት አካባቢዎች ያሉ ወረዳዎች እና ከተማ አስተዳደሮች ለመከላከያ ሠራዊቱ የሚያደርጉትን የደጀንነት ድጋፍ እንደተጀመሩ ገልጸው፤ ተጠንክሮ እንዲቀጥልም ጥሪ አቅርበዋል። ድጋፉ የሞራል እና የስንቅ አቅርቦት ሊሆን ይገባል ብለዋል። ሕዝቡ መረጃን ከተረጋገጠ የመረጃ ምንጭ ብቻ በመውሰድ የጠላት የሃሰት ፕሮፓጋንዳ ሰለባ እንዳይሆንም አሳስበዋል።

ከተሞች ደረጃቸውን የሚመጥን የደረጃ ሽግግር ያስፈልጋቸዋል ያሉት የአማራ ክልል ርእሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ ፤ ወልድያ የፍቅር፣ የታሪክ፣ የመገናኛ እና የንግድ ማዕከል የሆነች ከተማ ናት። የደረጃ ሽግግሩ ውብ፣ ጽዱ፣ የምትለማ እና በእቅድ የምትመራ ከተማ እንድትሆን ያግዛታል ነው ያሉት።

ርእሰ መስተዳድሩ በመልእክታቸው በወልድያ ከተማ የተለያዩ የልማት ፕሮጀክቶች ከተጀመሩ ዓመታት ቢቆጠሩም እስካሁን አለመጠናቀቃቸውን ገልጸዋል። ዋና ዋና የልማት ፕሮጀክቶች በተለይም የከተማዋ የውበት መለያ የሆነው የአስፓልት ግንባታ በተያዘው የበጀት ዓመት ይጠናቀቃል ብለዋል። ቀሪዎቹ የልማት ፕሮጀክቶችም በፍጥነት እንዲጠናቀቁ የፌዴራል እና የክልል መንግሥታት በጋራ እየተነጋገሩ እንደሚሠሩም ርእሰ መስተዳድሩ ቃል ገብተዋል።

የደረጃ ሽግግሩ ካስፈለገበት ምክንያት አንዱ ከተማዋ ለነዋሪዎቿ የምትመች ከተማ እንድትሆን ለማድረግ መሆኑን ያወሱት ዶክተር ይልቃል፤ በቀጣይም ለሪጂዮ ፖሊታንት የሚመጥን የከተማ አስተዳደር አመራር ይሰየማል ብለዋል። አመራሩ ብቻውን ለውጥ እንደማያመጣ ገልጸው የከተማዋ ነዋሪዎች ከአመራሩ ጎን በመቆም ለእድገት እና ለውጥ አብሮ መሥራት እንደሚገባም አሳስበዋል።

# ትሕነግ ለትግራይ ...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

ተናግረዋል።

ቡድኑ ለትግራይ ሕዝብ ጠላት መሆኑን ከጊዜ ወደ ጊዜ በተለያየ መንገድ ይፋ እያደረገ መምጣቱን በመገንዘብ ወላጆች ልጆቻቸውን ወደ ጦር ሜዳ ባለመላክ ከእልቂት ሊጠብቋቸው ይገባል ብለዋል። ይህም ውሳኔው በእጃቸው እንዳለ ጠቁመዋል።

እንደ አቶ ሌንጮ ገለፃ፣ የዩክሬን ጦርነት የዓለምን ኢኮኖሚ የተፈታተነ ሲሆን እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሀገራትን ደግሞ ጦርነት የሰብዓዊና የንብረት ጉዳት ያስከትላል። ኢኮኖሚውንም ይጎዳዋል።

በጦርነቱ ምክንያት በተለይ ሰብዓዊ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ወገኖች ይበልጥ ተጎጂ እንደሚሆኑ ገልጸው፤ አሸባሪው ትህነግ ጦርነት የከፈተውም በትግራይን ሕዝብ ችግር ሊነግድ መሆኑን ተናግረዋል።

መንግሥት የሕግ የበላይነትን በማስከበር ረገድ በርካታ ስራዎችን ሊሰራ ይገባል ያሉት አቶ ሌንጮ፣ ለዚህም መንግሥት በሀገሪቱ ውስጥ የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ላይ አተኩሮ ሊሰራ እንደሚገባና በዚህም ሕግ የማስከበሩን ተግባር አጠናክሮ መቀጠል አለበት ብለዋል።

# ሕወሓት በሕዝብ ስም የገባን ነዳጅና...

**ከ1ኛው ገፅ የዞረ**

የፈጸመውን ዝርፊያ መንግሥት በፅኑ እንደሚያወግዝ ገልጿል።

ለትግራይ ሕዝብ የገባ የሰብዓዊ የነዳጅና የምግብ እርዳታ ላይ ሕወሓት ትናንት የፈጸመው ዝርፊያ ዳግም በቆቦና አካባቢው ላይ ለከፈተው ጥቃት ማስፈጸሚያ ሊጠቀምበት እንደሆነም መታወቁንም አገልግሎቱ ጠቁሟል።

ዘረፋው የተፈጸመው የሽብር ቡድኑ ለዳግም ጥቃት እየተዘጋጀ ባለበት ወቅት መሆኑን መንግሥት አስታውቋል።

ዓለም አቀፎቹ ተቋማት እንዳረጋገጡት የሕወሓት የሽብር ቡድን በመቐሌ ከፈጸመው ዝርፊያ ባሻገር ድርጊቱን ለማስቆም የሞከሩ የሰብዓዊ ዕርዳታ ባለሙያዎችንም ማሰሩንም አገልግሎቱ ገልጿል።

በተጨማሪም መንግሥት ባለፉት ወራት መንግሥት ወደ ትግራይ ክልል አስፈላጊው ሰብዓዊ ድጋፍ በአግባቡ እንዲደርስ ለማድረግ የተናጠል ተኩስ አቁም ከማድረግ ባሻገር ያልተቋረጠ የሰብዓዊ ድጋፍ በየብስም በአየርም እንዲቀርብ ሲያደርግ መቆየቱን በመግለጫው አስታውሷል።

መንግሥት ለግጭቱ ሰላማዊ መፍትሄን ለመስጠት እንዲሁም መተማመንን ለመፍጠር እንዲቻል የሰብዓዊ ድጋፍና መሰረታዊ አገልገሎትን ለማስጀመር የሚያስችሉ ዝግጅቶችን ሲያደርግ መቆየቱ ጠቁሞ፤ መንግሥት ለሰላም የወሰዳቸው እርምጃዎች በሙሉ በሕወሓት የሽብር ቡድን በኩል ተቀባይነትን እንዳላገኙ ገልጿል።

ከዚህም አልፎ ከቀናት በፊት የሕወሓት የሽብር ቡድን አባልና ደጋፊው የዓለም የጤና ድርጅት ዋና ዳይሬክተር፤ ዓለም አቀፉ ተቋም ለሁሉም ዜጋ በእኩል ማገልገል አለበት የሚለውን መሰረታዊ መርሁን ወደ ጎን በማለት ትግራይ ውስጥ ሰብዓዊ እርዳታን ለማከፋፈል የሚውል ነዳጅ እጥረት አለ በማለት ሃሰተኛ ውንጀላ ሲያቀርብ እንደነበር በመግለጫው አመልክቷል።

መንግሥት ከጦርነቱ ጅማሮ ሲገልጽ የቆየውንና የሕወሓትን ሰብዓዊ እርዳታን ለጦርነት የማዋል ወንጀል ገለልተኛ ዓለም አቀፍ ምርመራዎችም በተጨባጭ ያረጋገጡት ሃቅ መሆኑን አገልግሎቱ ገልጿል።

የተዘረፈው ነዳጅ እንዲመለስ፤ የሰብዓዊ እርዳታ አቅራቢ ድርጅቶች የቀረበላቸውን ማስረጃ ከግምት በማስገባት በሽብር ቡድኑ ላይ ግልጽ የሆነ ተጠያቂነትን እንዲያሰፍኑና ዓለምአቀፉ ማሕበረሰብ የሕወሓት የሽብር ቡድን በፈጸማቸው ወንጀሎች ተጠያቂ እንዲያደርጉ መንግሥት ጠይቋል።

በተጨማሪም ወደ ትግራይ የሚገባው ሰብዓዊ እርዳታ ለታለመለት ዓላማ መዋሉንና ለትግራይ ሕዝብ እየደረሰ መሆኑን ማስተማመኛ እንዲሰጥ ሲል መንግሥት አሳስቧል።

በሽብር ቡድኑ የተፈጸመው ለትግራይ ሕዝብ የገባ የሰብዓዊ እርዳታ ዝርፊያ ለመላው ዓለም ግልፅ በሆነ መልኩ የቡድኑን ማንነት ያሳየ ነው ያለው መግለጫው፤ ከሽብር ቡድኑ ታሪክ መረዳት እንደሚቻለው ሕወሓት ከ1970ዎቹ ጊዜ ጀምሮ ለትግራይ ሕዝብ ተብሎ የሚገባን ሰብዓዊ እርዳታን መዝረፍ የለመደ ከሰብዓዊነት ያፈነገጠ ወንጀለኛ ቡድን ነው ብሏል።

መላው ኢትዮጵያውያንን ባሳዘነ መልኩ ይህ የመንግሥት ማሳሰቢያ በዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ ዘንድ ሰሚ ሳያገኝ፤ ተገቢ የሆነ የተጠያቂነት እርምጃም በሽብር ቡድኑ ላይ ሳይወሰድ መቆየቱን አስታውሷል።

ሽብርተኝነት በምእራቡም ሆነ በተቀረው ዓለም ተቀባይነት እንደሌለው ሁሉ በኢትዮጵያም ፍጹም ቦታ የለውም ያለው መግለጫው፤ ሆኖም መንግሥት አሁንም ለሰላማዊ አማራጭ በሩ ክፍት መሆኑንና የሕወሓት የሽብር ቡድንም ዳግም እየፈጸመ የሚገኘውን ጥቃት አቁሞ ወደ ሰላማዊ ምክክር እንዲመጣ አሳስቧል።

ሕወሓት ይህንን የመንግሥትን የሰላም ጥሪ የማይቀበል ከሆነ መንግሥት ሀገራዊ ሉዓላዊነትንና የዜጎችን ደህንነት ለማረጋገጥ አስፈላጊውን እርምጃ ሁሉ እንደሚወስድ አስጠንቅቋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በትጥቅ ትግል፣ በመንግሥትነትም አሁንም አሸባሪው ሕወሓት ዘራፊ ነው

ሰላምን እንደ ጦር ይፈራዋል፤ የሕዝቦች አንድነትና መተባበር እንቅልፍ ይነሳዋል፤ የአገር አንድነትና ከፍታ ለእርሱ የሞት ያህል ያስበረግገዋል፤ ልማትና ብልጽግና ከእርሱ ሰብዕና ጋር በእጅጉ የተቃረኑ ጉዳዮች ናቸው፤ ለዚህም ከልማት ይልቅ ዘረፋን፣ ከፍቅር ይልቅ ፀብን፣ ከአንድነትና መተባበር ይልቅ መጠራጠርና መነጣጠልን፣ ከይቅርታ ይልቅ ቂምና በቀልን፣... ዋነኛ መለያው አድርጎ ሰብኳል፤ ኖሮበታል፡፡ ከጫካ ሽፍትነት እስከ መንግስት፣ ከመንግስትነትም እስከ ወንበዴነት ጉዞው አጋሮቹ አድርጎ የሙጥኝ ብሏቸዋል፤ የአሸባሪው የሕወሓት ቡድን፡፡

ይህ ቡድን ነፍጥ አንግቶ ጫካ ሲገባ የሃሳብ ድሃ፣ የሰላም ጠንቅ ሆኖ ነበር፡፡ ተነጋግሮ መግባባት፣ ተወያይቶ ሰላም ማምጣት ፈጽሞ ከእርሱ አዕምሮ ቦታ ስላልነበራቸው ነው፡፡ እናም ከመነጋገርና ችግሮችን በሰላም ከመፍታት ይልቅ፤ ነፍጥ ተሸክሞ ጫካ በመግባት አገርና ሕዝብን መውጋት ጀመረ፡፡ መውጋቱ ሳያንሰው እዋጋለታለሁ ያለውን ሕዝብ ልጆቹንም፣ ምግቡንም ነጠቀው፡፡ ሕወሓቶች ጫካ በገቡበት ወቅት የእርዳታ ገንዘብን ለመሳሪያ ግዥ የማዋላቸውን የቢቢሲ የአፍሪካ ዴስክ ኤዲተር የነበረው ማርቲን ፕላውት በወቅቱ ያጋለጠበት ዘገባ የዚህ አንድ ማሳያ ነው፡፡

ምክንያቱም በ1977 ዓ.ም በኢትዮጵያ በተለይም በትግራይ ክልል ተፈጥሮ በነበረው ድርቅ ሳቢያ ለተጎዱ ወገኖች ከምዕራባዊያን የተሰበሰበውን በሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር ሕወሓት ለተጎጂዎች አላደረሰም፡፡ ይልቁንም 95 ሚሊየን ዶላር በቀጥታ ለመሳሪያ ግዥ እንዳዋለው ነው ዘገባው ያጋለጠው፡፡ ይሄንንም በጊዜው የነበረውን መንግስት ለመጣል አቅም መፍጠሪያ ተጠቅሞበታል፡፡

ይህ የዘረፋና የክህደት ተግባሩ ታዲያ የጫካ ሕይወቱ ታሪክ ሆኖ መቅረት አልቻለም፡፡ ይልቁንም እስከ አራት ኪሎ ቤተመንግስት በዘለቀው የስልጣን ጉዞው ቀጠለ፡፡ በዚህም በ27 ዓመታት የመንግስትነት ዘመኑ ዘረፋና ክህደት ሲፈጽም፤ በሕዝብ ስም የተበደረውን ዶላር መልሶ ሲያሸሽና ሲበዘብዝ፣ ለቡድኑና ግለሰቦች መበልጸጊያ ሲያውል፤ በአንጻሩ በሚሊዬኖች የሚቀጠሩ ዜጎች ኑሯቸው በእለት ድጋፍ ላይ እንዲመሰረት አድርጎ ኖሯል፡፡ መጠነ ሰፊ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ሲፈጽም፤ ዜጎች እርስ በእርሳቸው እንዳይተማመኑና በጋራ እንዳይቆሙ ጥላቻ፣ መለያየት፣ ቂምና በቀልን ዘርቷል፡፡

የመንግስትነት ዘመኑ በሕዝብ በቃህ ባይነት ሲነጠቅና ለሰራው ክህደት ተጠያቂ እሆናለሁ ብሎ ሲሰጋ፣ ቀድሞ በስሙ ሲዘርፍ፣ ልጆቹንም ምግቡንም ሲትነጥቀው ወደነበረው የትግራይ ክልል ሕዝብ "ትግራይን ላለማ መጣሁ" በሚል የቅጥፈት ዲስኩር ገብቶ ተሸሸገ፡፡ መንግስትም ለቡድኑ ልዩነቶች በንግግር ይፈቱ የሚል ተደጋጋሚ ጥሪ አቀረበ፤ የሃይማኖት አባቶችን፣ የአገር ሽማግሌዎችን፣ የሰላም እናቶችን ጭምር እንዲያግባቡ ለማድረግ ላከ፡፡ ሆኖም ቡድኑ ህልውናው የሚቀጥለው ከሰላም፣ ከልማትና አብሮ ከመኖር ሳይሆን፤ ከዘረፋ፣ ክህደትና ለዚህ ምቹ ሁኔታን ከሚፈጥረው ጦርነት በመሆኑ ዳግም የጦርነት ድግስ አዘጋጀ፤ አገርና ህዝብንም ክዶ የባንዳነት ተግባሩን በሰሜን እዝ የመከላከያ ሰራዊት ላይ ፈጸመ፡፡

ይሄን ተከትሎ አገርና ሕዝብ ለህልውና አደጋ እንዲጋለጡ፤ በተለይ ደግሞ የትግራይን ሕዝብ ለከፋ ስቃይና እንግልት ዳረገ፡፡ መንግስት ለሰብዓዊነት ቅድሚያ በመስጠት የሚያደርጋቸውን የተናጠል ተኩስ አቁሞችና የሰላም ጥሪዎች ጆሮ በመንሳት ይባስ ብሎ ለወረራ ወደ አማራ እና አፋር ክልሎች ተሰማራ፡፡ በዚህም አገርና ህዝብ ካጅነቱን፤ ዘራፊነትና አውዳሚነቱን ያረጋገጠባቸውን የግፍ ተግባራት ዳግም ገለጠ፡፡ ለሰብዓዊ ድጋፍ የሚላኩ የህጻናት አልሚ ምግቦችን ሳይቀር ከህዝብ ጉሮሮ ነጥቆ ለተዋጊ ሃይሎች ማዋሉን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎች በምርኮኛ የጦር መኮንኖቹ እጅ ሳይቀር በገፍ ተገኘ፡፡ ምንም እንኳን የወረራና አገር የማፍረስ ቅዠቱ በኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች የመከነ ቢሆንም፤ የፈጸመው ክህደት እና ዘረፋ ግን ታሪክ የሚዘነጋው አይደለም፡፡

ሽንፈትና ውርደት የማይሰለቸው ይህ ቡድን፣ ከመከነው ወረራውና አገር የማፍረስ ተልዕኮው ማግስት ወደ ትግራይ ክልል ድጋፍና እርዳታ እንዳይገባ በማደናቀፍ የትግራይ ህዝብ ለከፋ እንግልት እንዲዳረግ በማድረግ የዓለም አቀፉን ማህበረሰብ ትኩረት ለማግኘትና አይዞህ ባይ አጋሮቹን ከጎኑ ለማሰለፍ ሞከረ፡፡ ሆኖም በመንግስት በኩል የነበረው የሕዝብ ወገንተኝነትና ለሰላም ቅድሚያ የመስጠት ጥረት ያሰበው ሳይሳካ ሰብዓዊ ድጋፍ በአየርም በምድርም እንዲደርስ ሆነ፡፡ የሰላም ጥሪውም ቀጠለ፤ የሰላም ተደራዳሪ ቡድን ተሰይሞም የማደራደር ሚናው ለአፍሪካ ህብረት ሰጠ፡፡ ይሁን እንጂ ሰላም የማይሻው ዘራፊ ቡድን የሰላም ጥሪውን በቅድመ ሁኔታ ማጠር እና የፀብ ቀዳዳዎችን መፈለግ ጀመረ፡፡

በዚህም ለሰላም የተዘረጋውን እጅ ከፍቶ ሌላ ዙር የጦርነት እሳት ለኮሰ፤ በህዝብ ስም ወደትግራይ የገባውን የሰብዓዊ ድጋፍም ከህዝብ ነጥቆ ለተዋጊዎቹ ሰጠ፡፡ በእሱ እጅ ያልገቡትንና በግብረ ሰናይ ድርጅቶች መጋዘን ያሉ ሃብቶችንም እንደለመደው መዝረፍ ያዘ፡፡ ሕወሓት እንደ ትናንቱ ሁሉ ለትግራይ ሕዝብ ወደክልሉ የሚገባውን የሰብዓዊ ርዳታ (የምግብና ሌሎች ድጋፎችን) ለህዝብ ከማድረስ ይልቅ ከዓለም ምግብ ፕሮግራም መጋዘን በግልጽ እየዘረፉ መሆናቸውን የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ይፋ አድርጓል፡፡

ተመድ ይፋ እንዳደረገው የአሸባሪው ሕወሓት ታጣቂዎች መቀሌ ከሚገኘው የዓለም ምግብ ፕሮግራም መጋዘን ውስጥ ያለን 570 ሺ ሊትር ነዳጅ ዘርፏል፡፡ ታጣቂዎቹ የፈጸሙትን ዝርፊያ በቦታው የነበሩ የመንግስታቱ ድርጅት እርዳታ ሰጪዎች ለማስቆም ቢሞክሩም አልተቻላቸውም፡፡ የተዘረፈው ነዳጅ የእርዳታ ምግብ፣ የአፈር ማዳበሪያ እና ሌሎች የሰብአዊ እርዳታ ቁሳቁሶችን ለማጓጓዝ የሚውል የነበረ እንደመሆኑም፤ ድርጊቱ የሰብዓዊ ድጋፉ ሥራውን እንደሚያስተጓጉለውም ነው የተገለጸው። ይህ ለሕወሓት አዲስ ያልሆነ ከመንግስትነት እስከ ወንበዴነት ዘመኑ ሲፈጽመው የኖረው ተግባር ነው፡፡ ምንም እንኳን የሕወሓት ቡድን በዚህ መልኩ የክህደት ተግባር ውስጥ ቢሆንም፤ መንግስት ግን ዛሬም ለሰላማዊ ንግግር በሩን ክፍት አድርጎ እየጠበቀ ነው፡፡

ኢፕድ

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# የመገናኛ ብዙሃን ውጤታማነት ለአገራዊ ምክክሩ ስኬት

ታምራት ተስፋዬ

ኢትዮጵያ በየዘመኑ የተፈጠሩና ከዘመን ዘመን እየተሸጋገሩ የመጡ ያልተቋጩ ሃሳቦች፣ በይደር የቆዩ አለመግባባቶች እንዲሁም አገር ትቀጥል ዘንድ ቅድሚያ ተነስቷቸው የቆዩ የማያግባቡ አጀንዳዎች የተሸከመች አገር ናት።

አገሪቱ ልዩነቶችን በውይይት የመፍታት የቆየ ባህል ቢኖራትም እነዚህን ባህሎች በአግባቡ የመጠቀም ልምዱ ቀስ በቀስ እየጠፋ መጥቷል። ይህ ደግሞ ችግሮች በቀላሉ ፈጣን ምላሽ እንዳያገኙ፣ ውስጥ ውስጡን እንዲብላሉና ከትላንት እስከ ዛሬ እንዲከተላት ምክንያት መሆኑ በተደጋጋሚ ሲነገር ቆይቷል። ይሁንና ከህልውና ባሻገር ስለ መፅናትና መቀጠል እንዲሁም ስለሁለንተናዊ እድገት ሲታሰብ ለእነዚህ ልዩነቶችና አጀንዳዎች መፍትሄ መስጠት የግድ ይላል።

በአሁን ወቅት ኢትዮጵያ ዛሬ ላይ ከትናንት ሲንከባለሉ የመጡና በአገር ግንባታ ሂደቱ ላይ የራሳቸውን እክል የሚፈጥሩ ጉዳዮችን በምክክርና ውይይት ለመፍታት ከፍ ያለ ሥራ ጀምራለች። አገራዊ የምክክር ኮሚሽን በሕግ በማቋቋምና ኮሚሽነሮችን በመሰየም ወደ ሥራ ተገብቷል። ዋናውን የምክክር ሂደት ለመጀመር የሚያስችሉ የቅድመ ዝግጅት ተግባራትም በመከናወን ላይ ናቸው።

አካታች አገራዊ ምክክሩ በሁሉ ረገድ የሰመረ እንዲሆንም የተለያዩ ባለድርሻ አካላት ሚናቸው ግዙፍ ነው። የመገናኛ ብዙሃንም ነጻ፣ ገለልተኛ፣ ሚዛናዊና ወቅታዊ መረጃዎችን ተደራሽ ከማድረግ እና ሁነትን ከመዘገብ በዘለለ ለምክክሩ ስኬታማነት ከባድና ድርብ ኃላፊነት አለባቸው።

በዓለም አቀፍ ደረጃ አገራዊ ምክክር በማድረግ የተሳካላቸው አገራት እንዳሉ ሁሉ ምክክሩ ሳይሳካላቸው የቀሩ አሉ። ለዚህ ደግሞ ሚዲያው እንደ ዋነኛ ምክንያት የሚጠቀስ ነው። ይህ ታሪክ እንዳይደገም ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ መገናኛ ብዙሃን በሌሎች አገራዊ ጉዳይ ላይ ያሳዩትን ወገንተኝነት በአገራዊ ምክክሩ ላይም መድገም በተለይም ለጉዳዩ ሰፊ ሽፋንና ከመስጠት ጀምሮ ተግባቦት ላይ ጠንካራ ሥራ ይጠበቅባቸዋል።

ከሁሉ በላይ ሙያዊ ነጻነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የአካታች አገራዊ ምክክሩን አስፈላጊነት፣ ታላቅነትና ክስተትነት አምነው በመቀበል ለጉዳዩ ልዩ ትኩረት ሊሰጡት ይገባል። ምክክሩ አገራዊ እንደመሆኑ መጠን በተሻለና ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲከናወን ሂደቱን ከመዘገብ፣ መረጃ ከመስጠትና የተለያዩ ሃሳቦች እንዲንሸራሸሩ መደላድል ከመፍጠር ጨምሮ የመሪነት ሚናን በመጫወት ይዘታቸውን አገራዊ ጥቅምና ሰላም ላይ ማድረግ የግድ ይላቸዋል።

በምክክር ሂደቱ ላይ የሚነሱ ሃሳቦችን ለማንቋሸሽና ለመግፋት ከሚደረጉ ጥረቶች፤ በጽንፈኝነት የሚወጡ ሃሳቦችን ሌሎች ላይ ከማራገፍ እንዲሁም የአንድን አካል ሃሳብ ባልተገባ መንገድ ከመጠቀም የመቆጠብ ግዴታ አለባቸውም። የራሳቸው አጀንዳ ከመስጠትና አላስፈላጊ ጥብቅና ከመቆም፣ ሃሳብ ከማጠርና አስተሳሰብን ከመገደብ መቆጠብ እንዲሁም ብዝሃነትን የሚቀበሉና ጽንፈኝነትን የማያራግቡ መሆንም አለባቸው።

በእርግጥ መገናኛ ብዙሃኑ የየራሳቸው አላማ፣ አሰራር አቋምና እይታ አላቸው። ይሁንና ደግሞ ምክክሩን ውጤታማ ለማድረግ እንደ አገር ማሰብና መስራት የግድ ነው። ይሁንና አሁን ባለው የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን አደረጃጀትና አሰራር እንደ አንድ ማሰብ አስቸጋሪ የሚሆንበት አግባብ አለ።

በአገራዊ ውይይቱ ላይ መገናኛ ብዙሃኑ በባለቤትነት እንደያዛቸው አካልና ሌላም ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች ዘርን፣ አካባቢን፣ ሃይማኖትን ወይም ሌላ ቡድናዊ እሳቤን ተከትሎ የመንጎድ አዝማሚያዎች ሊያስመለክቱ ይችላሉ። ለአብነትም፣ የክልል መገናኛ ብዙሃንን የምክክር አጀንዳዎችን ከሚገኙበት ክልል እሳቤ ጋር ብቻ ማቆራኘት ሊታይባቸው ይችላል።

ይህን ለዚህ ችግር መፍትሄ ለመስጠት ታዲያ አገራዊ ምክክር በምን አይነት የሚዲያ ሞዴል ሊተገበር ይገባል የሚለው ከወዲሁ ሊጤን ይገባል። መገናኛ ብዙሃኑ የሚመሩበት ዝርዝር መመሪያ ሰነድ መዘጋጀትም ይስፈልጋል። ይህ ሲባል ግን የሚዲያ ነፃነት መጋፋት ማለት አይደለም። ይልቁንም አገራዊ ጥቅሞችን ከግምት ውስጥ ከማስገባት የመነጨ መሆኑ መዘንጋት አይኖርበትም።

በብሔራዊም ሆነ በክልል ደረጃ የሚገኙ መገናኛ ብዙሃን ምክክሩን ውጤታማ ለማድረግ ሁነቱን በመዘገብ ሂደት የሙያውን መርህ እና ስነምግባርን ባከበረ መልኩ መስራትና ከተለያየ የፖለቲካ፣ የሃይማኖትም ሆነ የብሔር ተጽእኖ ራሳቸውን ነፃ ማድረግ አለባቸው።

ከቡድንና አካባቢያዊ ልሳንነት ይልቅ የሁሉም ድምጽ ሆነው፤ የጎጥ ጥቅምን ለማስጠበቅ መሣሪያ ከመሆን መቆጠብ እና አገርን አስቀድመው ስለ አገር ክብርና ከፍታ እያሰቡ መሥራት ይጠበቅባቸዋል። መገናኛ ብዙሃኑ በነጻነት መስራት የሚችሉበትን አግባብ ለመፍጠርም አዋጆች፣ ህጎችና አደረጃጀታቸው መፈተሽ በተለይም ከፖለቲካም ሆነ በኢኮኖሚ ተፅእኖ ነጻ የሆነ አደረጃጀት እንዲይዙ ማድረግ ያስፈልጋል።

ከመደበኛ የመገናኛ ብዙሃን ፈተና ባሻገር የዲጂታል ሚዲያው ለአገራዊ ውይይቱ ከባድ ራስ ምታት ሊሆን እንደሚችል መገመት አይከብድም። ምክንያቱ ደግሞ በመደበኛው መገናኛ ብዙሃን መፈፀም የማይቻሉ ተግባራት ለአብነት ሀሰተኛ እንዲሁም ፀብ ቀስቃሽ የሆኑና በጥላቻ የተሞሉ መረጃዎችን በዲጂታል ሚዲያ ሊፈፀሙ ይችላሉና ነው።

በኢትዮጵያ ባለፉት 30 ዓመታት የተቀመሩ የፖለቲካ ትርክቶችና የተረጩ መርዞች በአሁን ወቅት ለማኅበራዊ ትሥሥር ገፆች ትልቅ ግብዓት ወደ መሆን አዝማሚያ ሄደዋል። ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ ያሉ የኢትዮጵያን መልካም የማይፈልጉ አካላት በዲጂታል መንገድም ሆነ በአካላዊ ጦርነት ኢትዮጵያን ለማጥቃት ያላሰለሰ ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ።

አብነትም አሮሞ ሳይሆኑ የኦሮሞ ሥም ገፆችን በመክፈት፤ አማራ ሳይሆኑ የአማራ ሥም የያዘ ገፅ በመክፈት የብሔር ጉዳዮችን አንስቶ በመሳደብና ተቆርቋሪ በመምሰል በሐሰተኛ ገፅ ተጠቅመው ህዝብን ከህዘብ የሚያቃቅሩ አስተውለናል።

በአርቲስቶች፣ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችና በሌሎች ታዋቂ ሰዎች ስም በርካታ ሐሰተኛ የትሥሥር ገፆች ተከፍተው ሲሠሩ ታይቷል። ሐሰተኛ የትሥሥር ገፆች ብቻ ሳይሆኑ ትክክለኛ አካውንቶች ሆነው ጭምር ትክክለኛ ያልሆኑ መረጃዎችን የሚያሰራጩ እንዳሉ እሙን ነው። እንደ መደበኛ በቀላሉ መቆጣጠር የሚቻል አለመሆኑ ደግሞ የማህበራዊ ሚዲያውን ስጋትነት ይበልጥ ያገዝፈዋል።

ይሁንና መደበኛው መገናኛ ብዙሃን ጠንካራ ሆነው መውጣትና እውነተኛ መረጃ ለህዝብ ተደራሽ የማድረግ አቅምን መፍጠር ከቻሉ በዲጂታል ሚዲያው የሚሠራጨው ሃሰተኛ መረጃ ማዳከም ቀላል ይሆናል። መረጃ የማግኘት መብትን በእጅጉ ቀላልና ቀልጣፋ ማድረግ በተለይም የህዝብን የመገናኛ ብዙሃን መሰረታዊ እውቀት ወይንም ሚዲያ "ሊትሬሲ" ማጎልበት፣ መረጃ በሚመለከት አስተዋይ፣ ጠንቃቃና ፈታሽ እንዲሆኑና በተሳሳተ አረዳድ፤ ያልተፈለገ ተግባር እንዳይፈፅሙ ማንቃት የግድ ይላል።

የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣንም በአገራዊ ምክክሩ ላይ የሚተላለፉ ዘገባዎችን መሰረት በማድረግ በመገናኛ ብዙሃኑ አሰራር ላይ ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል። እንደ ተቋም የመገናኛ ብዙሃንና የማህበራዊ ሚዲያዎችን መቆጣጠር የሚያስችል ረቂቅ ሕግ ፈጥኖ ማዘጋጀትም መተግበር ይጠበቅበታል።

### የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ፣ የወልዲያ ከተማን ከፈርጀ አንድነት ወደ ሪጂዮ ፖሊታን ደረጃ መሸጋገርን አስመልክቶ ትናንት በወልዲያ ከተማ በተዘጋጀ መርሃ ግብር ላይ ተገኝተው ያስተላለፉት መልዕክት

# "መንግሥት ለሰላም እጁን የዘረጋ ቢሆንም፤ በጦርነት ተወልዶ በጦርነት ያደገው ወያኔ የሰላምን አማራጭ ገፍቶ ጦርነት ከፍቷል"

- ዶክተር ይልቃል ከፋለ፣
የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር



ከጦርነት እና ዘረፋ ውጪ መኖር የማይችለው የሕወሓት ቡድን፣ አገርና ሕዝብን ክዶ የባንዳነት ተግባሩን ለመፈጸም በአማራ እና በአፋር ክክሎች ለወረራ በተሰማራበት ወቅት መዳረሻው ካደረጋቸውና የጥፋት በትሩን ካሳረፈባቸው አካባቢዎች የሰሜን ወሎ ዞን አንዱ ነው። የዞኑ ዋና ከተማ ወልዲያ ደግሞ ራሷን በወራሪው ላለማስደፈር ብርቱ ትግል ካደረጉ አካባቢዎች ግንባር ቀደሟ ነበረች። ይሄን ተከትሎም ወራሪው የሕወሓት የሽብር ኃይል ከተማዋን በከባድ መሳሪያ ጭምር ደብድቧል፤ ኋላ ላይም በርካታ መሰረተ ልማቶቿን አውድሟል፤ የግለሰብና የመንግሥት ንብረቶችን ዘርፏል፤ ትምህርት ቤቶችን፣ ሆስፒታሎችን፣ ዩኒቨርሲቲዎችንና ሌሎች የሕዝብ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ከአገልግሎት ውጪ አድርጓል።

በዚህ መልኩ ከስድስት ወራት በላይ በወልዲያ የጥፋት በትሩን ሲያሳርፍ የቆየው ይህ ቡድን፣ በሕዝቦች የተባበረ ክንድ ተመትቶ ወደነበረበት ጎሬ እንዲገባ በተደረገ ማግስት፤ ከተማዋ ከቁዘማ ይልቅ ወደ አዲስ ምዕራፍ ለመሻገር ብርቱ ጥረት ስታደርግ ቆይታለች። ለዚህ ደግሞ የከተማው፣ የዞኑ እንዲሁም የክልሉ አመራር ሰፊ ስራ ያከናወነ ሲሆን፤ ይሄም ከተማዋን ወደተሻለ ደረጃ ከፍ እንድትል እና ከፈርጀ አንድነት ከተማነት ወደ ሪጂዮ ፖሊታን ደረጃ ለመሸጋገር እድል ፈጥሮላታል። ይሄንን የሽግግር በዓሏንም ትናንት ያከበረች ሲሆን፤ በመርሃ ግብሩ ላይ የተገኙት የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ፣ ሽግግሩን ከወቅታዊው አገራዊ ሁኔታ ጋር በማያያዝ የሚከተለውን መልዕክት አስተላልፈዋል።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ያለባትን ድህነት ለማስወገድ ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴ እያደረገች፤ መሰረታዊ ለውጥም እያስመዘገበች የምትገኝ ሀገር ናት። የአማራ ክልልም የራሱን ድርሻ በልዩ ልዩ መስኮች እያከናወነ ይገኛል። ሆኖም ግን ይሄን የማይወደው፣ በጥላቻ ተጽንሶ በጥላቻ ያደገው፣ በጦርነት ተጸንሶ በጦርነት ያደገው፣ ወራሪው ወያኔ ቡድን ከፍተኛ ዝግጅት አድርጎ አማራ ክልልን እና አፋር ክልልን ባለፈው ዓመት መውረሩ የሚታወስ ነው።

በዚህ ረገድ የሰሜን ወሎ ሕዝብ ባጠቃላይ፤ ወልዲያ ከተማ በተለይ ያደረጋችሁት የጀግንነት እና ታሪካዊ መስዋዕትነት፤ ነጻነታቸውን ላለማስደፈር በየአካባቢው እንደ ድሬ ሮቃ፣ እንደ ዞብል፣ እንደ ወርቂት ከፍተኛ ተጋድሎ እያደረጉ ነጻነታቸውን የጠበቁትንም አንረሳቸውም። በመላው ኢትዮጵያውያን ትግል፣ በጀግናው መከላከያ ሠራዊታችን፣ የክልሉ ጥምር ኃይላችን ባደረገው ቅንጅት መረራው የወያኔን አከርካሪ በመምታት መቀልበሱ የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው።

ከዛም በኋላ ያለ ጦርነት መኖር የማያውቀው ወራሪው የወያኔ ቡድን የጦርነት ነጋሪት እየጎሰመ በየጊዜው ወረራ ፈጽማለሁ ሲል መቆየቱም የሚታወቅ ነው። ባለው መሰረት ያለ ጦርነት መኖሩ እውን በመሆኑ አሁንም ራሱ ወረራ ለመፈጸም ጦርነቱን በሰሜን ወሎ ዞን ከፍቷል። በዚህ ቅጽበትም ጀግናው መከላከያ ሠራዊት፣ ጀግናው ልዩ ኃይላችን፣ የአካባቢው ጥምር ኃይል መስዋዕትነት እየከፈለ ወረራውን እየመከተ ይገኛል።

ይሄን ወራሪ ቡድን አሁንም የበለጠ ተደራጅተን ባለፈው አከርካሪውን መትተን ወረራውን እንደቀለበስነው ሁሉ፤ ዛሬም የጋራ ትግል የአንድነት ትግል ይጠይቃል። መላው ኢትዮጵያውያን፣ የክልላችን ሕዝቦች፣ ልክ እንዳለፈው ጊዜ ልዩነታችንን ወደጎን በመተው በአንድነት ሆ ብለን ለመከላከያ ኃይላችን እና ለጥምር ኃይላችን ደጀንነታችንን ማስመስከር ይገባል። በዚህ ረገድ የአማራ ክልል የፀጥታ መዋቅር በሙሉ በየትኛውም አካባቢ ያለ ይሄን ወረራ ለመመከት በተጠንቀቅ ላይ ይገኛል። ይህን በመረዳት መላው ሕዝባችንም ይህን ወረራ ለመቀልበስ በአንድነት ተዘጋጅቶ እንዲጠብቅ በዚህ አጋጣሚ መልእክቴን አስተላልፋለሁ።

ሥራችን የሚሆነው ወያኔ ወራሪው ቡድን እስካልጠፋ ድረስ በአንድ እጃችን ክላሻችንን በሌላ እጃችን ልማታችንን በማድረግ እኩል ትኩረት ሰጥተን መሥራት ይጠበቅብናል። የጸጥታው ኃይላችን የሚችለውን ሁሉ መስዋዕትነት እየከፈለ እና ወረራውን እየመከተ ይገኛል። ይህ ጀግናው የጸጥታ ኃይላችን ከጎኑ ሆነን በደጀንነት ልበ ሙሉ ሆኖ እንዲዋጋ፤ እንዲመክት ብሎም ይህንን ወራሪ ቡድን እንዲያጠፋ መደገፍ ይኖርብናል። ድጋፋችን በተለያየ መንገድ የሚገለጽ ነው። ሞራል በመስጠት፣ ወኔውን በማነሳሳት፣ ስንቅ በማዘጋጀትና በማቅረብ፣ የመሳሰለው ነገር የደጀንነቱ መግለጫ ነው። በመሆኑም ሕዝባችን ይህን አውቆ ስንቅ በማዘጋጀት፣ የሞራል ድጋፍ ለመስጠት ሁሌም ዝግጁ ሆኖ መግለጽ ይገባዋል።

በቅርብ ርቀት ያሉ የዞንና የከተማ አስተዳደሮች ለጸጥታ መዋቅራችን ድጋፍ ማድረግ ጀምረዋል። በመሆኑም ድጋፉ ተጠናክሮ በሁሉም አካባቢ 24 ሰዓት እየተዋጋ ለሚገኘው የጸጥታ ኃይላችን ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል። ይህን የጸጥታ መዋቅር እንቅስቃሴ ለመደገፍ ልማታችንንም ለአንድ አፍታ ሳንዘነጋ መሥራት ይገባናል። ከልማታችን በብዙ መልኩ በሚገለጽ ደረጃ ራሳችንን ለመቻል ከድህነት ለመውጣት፣ ሥራ አጥነትን ለመቀነስ፣ የኑሮ ውድነትን ለማሻሻል የሚያስችሉ እርምጃዎችን መውሰድ ይገባናል።

ይህን በአግባቡ ለመውሰድም በየአካባቢው የሚገኙ የከተማ አስተዳደሮች ደረጃቸውን የሚመጥን እድገት እያገኙ መሄድ አለባቸው። ደረጃቸውን የሚመጥን የደረጃ እድገት ባገኙ ቁጥር የአካባቢው አመራር ከተሞች ውብ፣ ጽዱ፣ የሚለሙ እና የኢኮኖሚ፣ የትራንስፖርት፣ የመረጃ ማዕከል ሁነው እንዲመጡ ራሱን የቻለ በቂ አመራር ለመስጠት ያስችለዋል። ከተሞችን ሪጂዮ ፖሊታን ደረጃ ማሸጋገር ደግሞ በተለየ መንገድ ሥልጣንን ያልተማከለ በማድረግ፣ በእቅድ የሚመራ ለነዋሪዎች ምቹ የምትሆን፣ ውብና ጽዱ ከተማ፣ በእቅድ የምትመራ ከተማ መፍጠር የሚያስችል አመራር መገንባት ማለት ነው። የክልሉ መንግሥት በዚህ መንፈስ ወልዲያን የነበረ የፍቅር ከተማነቷን፣ የውበት ከተማነቷን፣ የትራንስፖርት መገናኛ ከተማነቷን፣ የልማት ማዕከል መሆን የምትችል ከተማነቷን የሚያሳድግ፣ የሚያስውብ፣ የሚመራ አመራር እንዲዋቀር ያደርጋል።

ሆኖም የክልሉ መንግሥት የሚያዋቅረው አመራር ብቻውን የሚያመጣው ለውጥ የለም። የሚዋቅረው አመራር ዋናው መሰረቱ፣ ደጋፊዎቹ የከተማው ነዋሪዎች ናቸው። ያለ ከተማው ነዋሪ ድጋፍ፣ ያለ ከተማው ነዋሪ አስተዋጽኦ፣ ያለ ከተማው ነዋሪ ቅንጅት ወልዲያ ከተማን አመራሩ በፈለገው መንገድ ማሳደግ እና ማሳመር አይችልም። በመሆኑም የከተማው ባለቤቶች እናንተ ነዋሪዎች ናችሁና በሪጂዮፖሊታን ከሚሰየመው አመራር ጋር እንደተለመደው ተቀናጅታችሁና ተባብራችሁ ወልዲያ ከተማችን የነበራትን ውብ ታሪክ፣ የፍቅር ታሪክ፣ የልማት ታሪክ አድሳችሁ እንድታስቀጥሉ አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

ከዚህም ባለፈ ከተሞች የሪጂዮፖሊታን ደረጃ አገኙ ማለት በራሳቸው የመልማት አቅም ደረጃ አገኙ ማለት ነው። በመሆኑም በገቢ አሰባሰብ፤ በውበትና ጽዳት አስተዋጽኦ፤ የራሳችሁን አስተዋጽኦ እንድታስቀምጡ አደራ ማለት እፈልጋለሁ። ከዚያ ባለፈ ወልዲያ ከተማ የተጀመሩ ብዙ መሰረተ ልማቶች ቢኖሩም አጥጋቢ ያልሆኑ፤ አንዳንድ የተጀማመሩ ፕሮጀክቶች ገና ያልተጠናቀቁ በመሆናቸው፤ የፌዴራል መንግሥትም የክልሉ መንግሥትም ልዩ ትኩረት አድርገን የምንሰራው የቤት ስራችን መሆኑን በናንተ ፊት ለማረጋገጥ እፈልጋለሁ። በመሆኑም ተባብረን በጋራ የተጀመሩትን ፕሮጀክቶች በተለይም ዋና ዋና ፕሮጀክቶች የከተማችን ገጽታ ሊቀይር የሚችለው የመህል መንገዱ በተቻለ ፍጥነት በዚህ ዓመት የሚጠናቀቅበትን ሁኔታ ለመፍጠር የምንሰራ መሆኑን ማረጋገጥ እፈልጋለሁ።

ከዚህ በተረፈ ልማታችን በተጀመረው ጦርነት የሚደናቀፍ አይሆንም። ስራችን እና አካሄዳችን አራት ዐይና በመሆን፤ ሁለት ዐይናችን በልማት፣ ሁለት ዐይናችን በሰላም ላይ በማድረግ ተባብረን አንድ ሆነን በመቆም የማንበገር ጀግና ሕዝቦች መሆናችንን በድጋሚ ማረጋገጥ እንደምንችል የሚጠራጠር ሰው ከቶ የለም። በመሆኑም አንድነታችንን እናጠናክር፤ የሚተማመኑበት የመረጃ ምንጭ ላይ መረጃ እንውሰድ፤ ማንኛውም ሕዝባችን በራስ የሚተማመን እንዲሆን የተረጋጋ እንዲሆን፣ ጽናት ያለው እንዲሆን፣ ቆራጥ እንዲሆን እርስ በርሳችን እንመካከር።

የእኛ ታሪክ ያለፈ ታሪካችን የጀግንነት ታሪክ ነው፤ የቆራጥነት ታሪክ ነው፤ የጽናት ታሪክ ነው፤ ሀገር የመገንባት ታሪክ ነው። ይሄ ታሪክ ዳግም በዚህ ትውልድ የሚሰራ ለመሆኑ ያየነው ስለሆነ ማንም ሊጠራጠር አይገባም። ስለዚህ የሰሜን ወሎ ሕዝብ በአጠቃላይ የአማራ ክልል ሕዝብ ለተከፈተብን ጦርነት የማንንበረከክ፤ ህልውናችንን በትግላችን የምናስከበር መሆኑን ካለፈውም ያሳየን ስለሆነ፣ አሁንም እንደምንደግመው በቆራጥነት እና በጽናት ሁሉም በአንድነት እንዲነሳ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

የገጠመንን ችግር በትግላችን እናሸንፋለን። ያለብንን የድህነት ችግር በትግላችን ልማቱን በማፋጠን ወደ ብልጽግና እንሸጋገራለን። ስኬት ያለ ትግል፣ ስኬት ያለ ውጣ ውረድ አይገኝምና ይህን ታሳቢ በማድረግ ሁላችንም እንጽና እንጠንክር። የመጨረሻዎቹ አሸናፊዎች እኛ ነን። ማንም ቢሆን ነጻነቱንና ህልውናውን በሌላ አገር ያረጋገጠ ሀገርም ሆነ ሕዝብ የለም። ህልውናችን በትግላችን እና በጽናታችን ብቻ ነው የሚረጋገጠው። ይሄን ታሳቢ አድርገን በአንድነት እንቁም። ከዚያ ባለፈ እየተወረርን፣ ሀብትና ንብረታችን እየወደመ፣ የውጭ ሀገር የሚዲያ ተቋማት ዲፕሎማቶች በተለየ ሁኔታ ትግራይን እንደወረርን እና እንዳስቸገርን ተደርጎ የተዛባ ወሬ የሚሰራጨው ትክክል አለመሆኑን እንዲያስቡት በድጋሚ በዚህ መድረክ መናገር እፈልጋለሁ።

የአማራ ሕዝብ ግማሽ አካሉ በወያኔ ቁጥጥር ስር ሆኖ ብዙ የሰው ሕይወት የጠፋበት፣ አካል የጎደለበት፣ ንብረት የተዘረፈበትና የወደመበት አካባቢ ነው። በምን ሂሳብ በምን ምክንያት የአማራ ሕዝብና የፀጥታ መዋቅር የትግራይን ሕዝብ እንደሚወርና እንደሚያሰቃይ ተደርጎ ሊተረክ ይችላል? ይሄን የተዛባ ትርክት፣ ይሄን የተዛባ መረጃ በአፅንኦት በመረዳት ሁሉንም በልኩ እንዲዘግቡ፣ እንዲናገሩ፣ እንዲፅፉ በድጋሚ ጥያቄያችንን እናቀርባለን።

የአማራ ሕዝብ ሰላም ፈላጊ ሕዝብ ነው። የአማራ ሕዝብ ሌላውን ለመውረር አልሄደም። የአማራ ሕዝብ ስለተወረረና ስለተጠቃ ብቻ የተነሳ ሕዝብ ነው። የአማራ ሕዝብ ህልውናው ስለተደፈረ ብቻ የተነሳ ሕዝብ ነው። ሌላውን ያለአግባብ ሂዶ ለመግደል፤ ሴቶችን ለመድፈር፣ ሀብት ንብረት ለማውደምና ለመዝረፍ የሄደበት የትኛውም አካባቢና ቦታ የለም። ይሄንን በግልፅ እንዲረዱት እንፈልጋለን።

አሁንም ቢሆን መንግሥት ለሰላም እጁን ዘርግቶ የሰጠ ቢሆንም፤ እንደልማዱ በጦርነት ተወልዶ በጦርነት ያደገው፣ የሰላምን አማራጭ ባለመከተል ጦርነት ራሱ የከፈተ መሆኑን እዲረዱት እንፈለጋለን። ጅራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ ይጮሃል እንዲሉ፤ መረጃውን አዘጋጅቶ ጦርነት በተከፈተ በደቂቃዎች ውስጥ መግለጫውን አውጥቷል። ይሄ የሚያሳየው ጦርነቱ በማን እንደተጀመረ ግልፅ አድርጎ ይመሰክራል። ስለሆነም የዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የአማራን ሕዝብ በዚህ መልኩ እንዲረዱት እንጠይቃለን። ተገቢ መረጃን የሚፈልጉ ከሆነ በየደረጃው ያለን ሰዎች ማብራሪያ ለመስጠት ዝግጁ ነን። ከዛ ባለፈ የባለፈው ደም ሳይደርቅ፣ የባለፈው ኀዘን ሳይረሳ ዳግም ወረራ ቢያደርጉ ስራችንን አናቋርጥም። የመልሶ ግንባታ ስራውን በተጠናከረ ሁኔታ እናስቀጥላለን።

ምናልባትም አንዳንድ ተቋማትን ከነበራቸው ደረጃ በተሻለ መንገድ መልሰን እንገነባቸዋለን። የተጎዱ የሕብረተሰብ ክፍሎቻችንን በምንችለው ደረጃ በማፅናናት የመደበኛ ሕይወታቸው ሳይስተጓጎል የምንችለውን ድጋፍ እናደርጋለን። ለዚህ የሚረዳ የፕሮጀክት ፅህፈት ቤት አዋቅረን የሰው ሃይል መድበን ስራ ከጀመርን ቆይተናል። ደግሞም እናደርገዋለን። ጊዜው በአንድ በኩል በችግር የተሞላ፣ ነገር ግን በትግል የምንፈታው መሆኑን ተስፋ ሰጪ ነው። ጊዜያችን ብሩህ ነው።

ወልዲያን የፍቅር ከተማነቷን የውበት ከተማነቷን የታሪክ ከተማነቷን የመገናኛ ከተማነቷን አጠናክረንና አስፍተን ለማስቀጠል የሪጅዮፖሊታን ከተማነት ደረጃ ከፍተኛ እገዛ ያደርግላታል ብለን እንጠብቃለን። ለዚህ ሁላችን እንትጋ። መጪው ጊዜ ተጠናክረንና አንድ ሆነን ከሄድን ፍላጎታችንን ለመሳካት ህልውናችንን ለማረጋገጥ ልማታችንን ለማፋጠን ብሩህ ነው የሚል እምነት አለኝ። ስለዚህ እንሰባሰብ፤ አንድ እንሁን እንደማመመጥ እንከባበር በአንድ አቅጣጫ እንመራ ይሄ ከሆነ መቼውን ቢሆን አሸናፊዎች ነን። የኢትዮጵያ ታሪክም ይሄንን ነው የሚያስረዳው። በመሆኑም የክልሉ መንግሥት ከወልዲያ ከተማ ጎን ሁኖ በማናቸወም እንቀስቃሴ አብሮ ተሰላፊ አጋዥ መሆኑን በዚህ መድረክ እያረጋገጥኩ፤ መልካም በአል እንዲሆንላችሁ እየተመኘሁ፤ እንኳን ደስ አላችሁ እላለሁ።

ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባረክ። መጪው ዘመን የሰላም የድል እንዲሆንልን እመኛለሁ። በድጋሚ መልካም በዓል፤ እንወዳቸኋለን፣ እናከብራችኋለን የፍቅር የውበት ከተማ ሁኑልን፤ እናመሰግናለን ወልዲያዎች።

# አገር በቀል እውቀት እና ወቅታዊ ይዞታው

**ግርማ መንግሥቴ**

የዛሬው ርእሰ ጉዳያችን አጠቃላይ አገር በቀል እውቀቶቻችን፣ አገራዊ እሴቶቻችን በምን አይነት ሁኔታ ላይ እንዳሉ፤ ለአገራዊ ችግሮች ምን አይነት መፍትሄዎችን እንካችሁ እያሉን እንደሆነ ... እንመለከታለን። ከሁሉም በፊት ግን መሰረቱ "አገር በቀል እውቀት" የሚለው ነውና እሱን እንበይን።

አገር በቀል እውቀት ማለት በውስን አካባቢዎች ላይ በኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ገጽታዎች ዙሪያ ላሉ ክፍተቶች መፍትሄ ይሆኑ ዘንድ ባህላዊ በሆነ መንገድ በአንድ ወይም በተወሰኑ ሰዎች የሚመነጭና የሚተገበር እውቀት ነው፡፡ በእንግሊዝኛው በዋናነት "Indigenous knowledge" የሚለው የሚገልፀው ሲሆን "Traditional knowledge" ወይም "Local knowledge" የሚሉትም ሊተኩት ይችላሉ። የማህበረሰብ እውቀት ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ የሕይወት ገፅታዎች የሚዳሰሱበትና መፍትሄ የሚሰጥበት የተገለፀና ያልተገለፀ እውቀትና ልምድን ያጠቃለለ ነው፡፡

በብዙ ዘመናት ልምድ የዳበረና በባህል ውስጥ ሰርፆ ከትውልድ ትውልድ በታሪክ፣ በዘፈን፣ በአባባል፣ በእምነት እና በሌሎች መንገዶች በአካባቢው ቋንቋ የሚተላለፍ እውቀት ነው፡፡ እውቀቶቹ በተገኙበት ቦታ ምንጭ ለሆኑት ግለሰብና ቤተሰብ የተሰጠ ልዩ ጥበብ ተብሎ የሚታወቅ ሲሆን በአብዛኛው ግን በጊዜ ሂደት በአካባቢው ማህበረሰብ እየተለመደና እየሰፋ ሲመጣ የማህበረሰቡ የጋራ ንብረት ይሆናል፡፡ እንደ አገራችን ባሉ በተፈጥሮ ሀብት በበለፀጉ አገራት በተለይ በግብርና፣ በጤና እና በአካባቢ ጥበቃ ዘርፎች የአገር በቀል እውቀቶች እና ቴክኖሎጂዎች ያላቸው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው፡፡ በተጨማሪም በትራንስፖርት ዘርፉ የአገር በቀል እውቀቶች እና ቴክኖሎጂዎች ወሳኝ ሚና አላቸው፡፡ በግብርናው ዘርፍ የእፅዋትና አዝርእት ተከላ፣ መረጣና አሰባሰብ ሂደት፣ በእንስሳት እርባታና አያያዝ ስርዓት እና ለመሳሰሉት ተግባራት መሠረት የሚሆን በግለሰብና በማህብረሰብ ውስጥ የዳበሩ ብዙ እውቀቶች አሉ፡፡ (hawassa online.com)

ለጠቅላላ ግንዛቤ ይህንን ከያዝን፤ በአገር በቀል እውቀት እነማ ተጠቃሚ ሆኑ፤ ምንስ አተረፉ የሚለውን ከመቃኘታችን በፊት፤ ከአገር በቀል እውቀት ክፍሎች፣ በተለይም በማይዳሰስ ቅርስነት የሚታወቀው ስነቃል መገለጫ ከሆኑት መካከል አንዱ ወደ ሆነው ጥንታዊ ፍትህ አሰጣጥ ስርአት እንሂድ።

የኢትዮጵያ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር (2009) ለንባብን ባበቃው ጥራዝ ውስጥ ተገልፆ እንደሚገኘው ከሆነ "ጥንታዊ ፍትህ አሰጣጥ ስርአት" ምድቡ ከ"የማይዳሰስ ባህላዊ ቅርስ" ሲሆን፤ "ባህላዊ የዳኝነትና የእርቅ ስርአቶች፤ ግጭቶችና አለመግባባቶች የሚፈቱበት ባህላዊ የእርቅ መንገድ ነው።" ፋይዳውም ማህበራዊ፣ አላማውም የፍትህ ስርአትን በማንገስ ግጭቶችን በማስወገድ፣ በሰላማዊ መንገድ በመፍታት አካባቢያዊና አገራዊ ሰላምን ማስፈን ... ወዘተ ነው።

አገር በቀል፤ የሰው ልጅ ወካይ የማይዳሰስ ቅርስ የሆነው «ጥንታዊ ፍትህ አሰጣጥ ስርአት» በድሮው ዘመን በችግር ፈቺነቱ የታወቀ ሲሆን፤ በተለይ በ«በላ ልበልሃ» የፍርድ ሂደት (የከሳሽና ተከሳሽ ምልልስ) መደበኛውን ፍርድ ቤት ተክቶ ይሰራ እንደ ነበር ይታወቃል።

ለዚህም፤

**በሳ ልበስሃ**

**የአፄ ሥርዓቱን፣**

**የመሠረቱን፣**

**የአብርሃም ራቱን፣**

**አልናገርም ሐሰቱን፣ ሁል ጊዜ እውነት እውነቱን።**


የሚለውንና ተደጋግሞ የሚመጣውን አዝማች ማስታወሱ በራሱ በቂ ሲሆን፤ ይህም በኢትዮጵያ ዘመናዊ ፍርድ ቤቶች ሳይቋቋሙና የወንጀለኛ መቅጫ እና የፍታብሄር ህግ ተረቆና በአዋጅ ፀድቆ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት ህዝቡ ለፍትህና ርትእ ስፍነት ሲጠቀምበት የኖረ፤ በአገር ሽማግሌዎች የሚዳኝበት ባህላዊ የፍርድ ሂደት ነው።

እንደ አጠቃላይ ብያኔም፤

"በላ ልበልሃ" እስካሁንም በተለይ ከከተሞች ርቀው በሚኖሩ የተለያዩ ብሄር ብሄረሰቦች እየተጠቀሙባቸው ከሚገኙት ባሕላዊ ሽምግልናዎች የተለየ የሚያደርገው መሰረታዊ ልዩነት ያለው የዳኝነት ስርዓት አለው፡፡ ይኸውም በዳይና ተበዳይ /ከሳሽና ተከሳሽ/ ዳኞች ፊት ቀርበው ክርክር የሚያደርጉት በስነ ግጥምና በቅኔ መሆኑ ነው፡፡ ህዝቡም ዙሪያቸውን በመታደም የፍርድ ሂደቱንና ክርክሩን የሚከታተል ሲሆን፤ በተለይ "በበላ ልበልሃ" ክርክር አሸናፊ የሆነ ሰው በሙግት አዋቂነቱና በግጥም ችሎታው ከህብረተሰቡ ከፍተኛ አድናቆትንና ከበሬታን ያገኛል፡፡

የሚለውን ብያኔ በጋራ መግባቢያነት መውሰድ ይቻላል። (ከ"በላ ልበልሃ" ጋር በተያያዘ የስለሺ ለማን "በላ ልበልሀ" መጽሐፍ መመልከት ተገቢ ይሆናል።)





ይህ መደበኛውን ፍርድ ቤት ተክቶ (ወይም በሌለበት) ሲያገለግል የኖረው ነባሩ «በላ ልበልሀ» የፍርድ ሂደት እንደ አገር በቀልነቱ ዘመናዊውን የፍርድ ሂደት ሲያግዝ አልታየም። እንደውም እንደ ኋላ ቀር አሰራር ተቆጥሮ ተወረወረ እንጂ ለፍትህና ርትእ አገልግሎት አልታጨም። ይሁን እንጂ፣ በአሁኑ ሰአት በአንዳንድ የአገራችን ክፍሎች ይህ «ጥንታዊ ፍትህ አሰጣጥ ስርአት» የህዳሴ ዘመኑ የመጣ ይመስላል። ወደዛ ከመሄዳችን በፊት ግን የአገራትንን ልምድ እንቃኝ።

አገር በቀል እውቀትን በተገቢው መጠን መጠቀም የቻሉ አገራት በርካቶች እንደሚሆኑ መጠራጠር አይቻልም። ይሁን እንጂ በግንባር ቀደምነት የሚጠቀሱ አገራት ደግሞ አሉ።

እንደ አገር ስንመለከተው ጃፓን የብዙዎችን ምስክርነትና እውቅናን አግኝታለች። ባህሏን ሳታስነካ፣ ማንነቷን አስከብራ ማደግ በመቻሏ በምሳሌነት እየተጠቀሰች ትገኛለች። ታይላንድና ጃፓን የመሳሰሉት አገራት በሳይንስና ምርምር አሁን ለደረሱበት የእድገት ደረጃ መሰረታቸው አገር በቀል እውቀት መሆኑን በርካታ ጥናቶች ያመለክታሉ፡፡ የቻይናን የተመለከትን እንደሆን ጉዳዩ ወደ ላይ ከፍ ብሎ እናገኘዋለን።

ቻይና አገር በቀል እውቀትን እንዲሁ እንደ ዋዛ የምትመለከት አይደለችም። አጥብቃ እንደ ያዘችው የኮንፊሺየስ አስተምህሮ ሁሉ አገር በቀል እውቀት ያፈራቸውን እሴቶች ሁሉ በከፍተኛ ደረጃ ወደ ተግባር በመቀየር፤ በተቋማት ደረጃ በማደራጀት ከራሷም አልፋ ወደ ሌሎች አገራት በማዛመት በከፍተኛ ደረጃ የጂዲፒዋ መደጎሚያ አድርጋዋለች።

እንግሊዝ በመንግስት ደረጃ አንድ ጠብሰቅ ያለ ስለ ባህላዊ ህክምና የሚያስተምር መጽሐፍ (ከኢትዮጵያ የዘረፈችውን ተርጉማ ነው የሚሉ አሉ) አሳትማ ለዜጎች አሰራጭታለች። እንዲህ እንዲህ እያልን ከሄድን የብዙ አገራትን ተሞክሮ ማየት እንችላለን።

አሁን ወደራሳችን እንምጣና አገር በቀል እውቀታችን ያለበትን ወቅታዊ ይዞታ እንመልከት።

ዛሬ ዛሬ አገር በቀል እውቀቶች እንዳይጠፉ መጠበቅ፣ እውቀትን ለትውልዱ በሚገባ በማስተማር ተጠቃሚ ማድረግ፣ የግብረግብ ትምህርትን በስፋት ማስተማር፣ ስለ እፅዋት ጥበቃና እንክብካቤ፣ ስለ መድኃኒት እጽዋት፣ ስለ ጥንታዊ ሥዕሎች አሳሳል፣ ስለ ቀለማት አቀማመም እና ስለ ጂኦሎጂ የድንጋይ ጥበብ ማስተማር አገራችን የተያያዘችውን የብልጽግና ጎዳና የሰመረ ለማድረግ የሚያግዝ መሆኑ በብዛት እየተነገረ ነው። በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሳይቀር ጉዳዩ የብዙዎች ርእሰ ጉዳይ እየሆነ ነው። በርካታ ጥናቶች እየቀረቡ መደረግ ያለበትን መደረግ ከሌለበት እየለዩ እያመለከቱ ይገኛሉ። ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴርም እየተነቃቃ ያለ ይመስላል።

ባለፈው አመት በወሎ ዩኒቨርሲቲ አገር በቀል እውቀት ላይ ያተኮረ 6ኛው ዓለም አቀፍ አውደ "ወረሸኝን ለመከላከልና ለአገር ሰላም ግንባታ" በሚል 19 የጥናትና ምርምር ስራዎች ቀርበው ነበር፡፡ በዚህ ጉባኤ ላይ የአገር በቀል ዕውቀቶች ለአገር ያላቸውን ፋይዳ የሚመለከቱ ጥናታዊ ጽሁፎች ቀርበዋል፡፡ መንግስትም ለአገር በቀል ዕውቀቶች ትኩረት መስጠቱም ተመላክቷል፡፡

ከአርት አኳያም አያልነህ ሙላት በአንድ ወቅት ከአርትስ ቲቪ ጋር ባደረጉት ተከታታይ ውይይት "ለችግሮቻችን መፍትሄው አገር በቀል እውቀት ነው" ሲሉ መደመጣቸውም ይህንኑ የአገር በቀል እውቀትን አስፈላጊነት የሚያሰርፅ ሆኖ ነው የምናገኘው።

ወደ ጎንደር ዩኒቨርሲቲም ስናመራ የምናገኘው ተመሳሳይ ሲሆን፤ መጋቢት 2011 «አገር በቀል እውቀትና ትምህርት በኢትዮጵያ፤ ፋይዳው፣ ተግዳሮቶችና የወደፊት አቅጣጫው" በሚል ርዕስ የጎንደር ዩኒቨርሲቲ የሥነ ትምህርት ፋካልቲ ያዘጋጀው አገር አቀፍ ዐውደ ጥናት ተካሄደ።» በሚለው የመገናኛ ብዙሃን ዘገባ "በዘመናዊው ሥርዓተ ትምህርቱ ውስጥ አገር በቀል እውቀትንና ትምህርትን በማካተት ምራልና ግብረገብ ያለው ትውልድ መቅረጽ እንደሚገባ ምሁራን አሳሰቡ፡፡" የሚል ተካትቶ ማንበባችን አይዘነጋም።

አላማውም "ጠቃሚ አገር በቀል እውቀትና ትምህርትን በጥናት በመለየት በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ የሚካተቱበትንና ለትውልድ የሚተላለፉበትን አመቺ ሁኔታ መፍጠር" እንደነበርም እንደዛው። (ይህን ስንል ነጋድራስ ገብረ-ሕይወት ባይከደኝ "መንግስትና የህዝብ አስተዳደር" በተሰኘው መጽሐፋቸው ላይ በአገራችን ስለሚገኙ ብሄራዊ ችግሮች ውስጥ ሙግትን በሚመለከት የፃፉት እንዳለ ሆኑ፤ የጠቀሷቸው ችግሮች እስከተፈቱ ድረስ ነው።)

በውይይቶቹም "አገር በቀል ዕውቀትን በዘመናዊ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ በይዘትና በማስተማሪያ ዘዴ ማካተት ይገባል፡፡"፤ "የአገር በቀል እውቀትና ትምህርትን ፋይዳ በሚገባ በመረዳት ሞራልና ግብረገብነትን የተላበሰ ኅብረተሰብ መፍጠር ያስፈልጋል፤" እስካሁን በአገሪቱ የተተገበሩት ሥርዓተ ትምህርቶች የአገሪቱን የኋላ ታሪክ ያላካተቱ፤ የወደፊት ጉዞዋን መሠረት ያላደረጉና ከምዕራባውያን የመጣውን በጭፍኑ የተቀበሉ" በመሆናቸው በአገር በቀል እውቀቶቻችን ሊተኩ ይገባል፤ ኢትዮጵያ "በሥነ ፈለክ፣ በሕክምናውና በማዕድን ጥናት ዓለምን የሚያስደምሙ እውቀት ነበሯት" ግን አልተጠቀመችበትም፤" አገር በቀል እውቀት አሁን ባለው ሥርዓተ ትምህርት ባለመካተቱ አገሪቱዋን ወደፊት መራመድ አልቻለም"፤

«የአገሪቱ ሥርዓተ ትምህርት ከመነሻው ለአገር በቀል እውቀት ትኩረት ያልሰጠ» መሆኑ፤ «ዘመናዊው የትምህርት ሥርዓታችን በምዕራባውያን ፍላጎትና ተጽእኖ የተቀረፀ በመሆኑ ከአገር በቀሉ እውቀትና ትምህርት ጋር ማጣመር» እንደሚያስፈልግ፤ «ስኬት አካባቢን በማወቅ የሚመጣ» በመሆኑ «አገር በቀል እውቀትን በሥርዓተ ትምህርቱ ውስጥ በማካተት መመርመርና ማጥናት» እንደሚያስፈልግ፤ «በባእዳን የተዘረፉ መጻህፍትና ቅርሶችን ማስመለስ፣ ያሉትን ጥበቃ ማድረግና መመዝገብ እንዲሁም በአገር በቀል ምሁራንና ተመራማሪዎች ጥናት እንዲደረግባቸው በማድረግ ለቀጣዩ ትውልድ ማሻገር እንደሚገባም»፤ «ለአዲሱ ትውልድ ቀደምት የነበረውን የመከባበርና የመረዳዳት ባህል በአገር በቀል እውቀትና ትምህርት ማዳበር» እንደሚያስፈልግ ... እና የመሳሰሉት በጥናቶቹ ላይ የተመሰረቱ አስተያየቶች ቀርበው እንደ ነበር ተገንዝበናል።

ከአዲስ ዘመን ጋር ቆይታ ያደረጉት፣ በኦሮሚያ ክልል የቡሶ ጎኖፋ ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ ገረመው አሊቃ እንደሚሉት የክልሉ መንግስት የገዳ ስርአት አካል የሆነውንና ባህላዊውን ቡሶ ጎኖፋ ወደ ዘመናዊነት አሳድጎ፤ በቢሮ ደረጃ አዋቅሮ ... ወደ ስራ ይግባ እንጂ፤ እንደ አገር ከታየ አገር በቀል እውቀቶቻችንን ገና አልተጠቀምንባቸውም።

ከላይ ዘመኑ የአገር በቀል እውቀታችን ህዳሴ ነው ስንል ያለ ምክንያት አለመሆኑን እነዚህ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት (አምቦና ሌሎች ዩኒቨርሲቲዎችንም ጨምሮ) እንቅስቃሴዎች ያሳያሉ ብለን እናስባለን። ይህ ማለት ግን አፍን ሞልቶ ሰርቷል በማስባል እጅና እግርን አጣጥፎ የሚያስቀምጥ ነው ማለት አይደለም። በተለያዩ መድረኮችና ሁኔታዎች «ገና ብዙ ይቀራል» እንደሚባለው አሁንም ገና ብዙ ይቀራል። አገር በቀል እውቀቶቻችን የሁላችንም እስኪሆኑ ድረስ፤ በሁላችንም ተቀባይነት እስኪያገኙ ድረስ፤ ተቋማዊ አደረጃጀቶች እስከኖሯቸው ድረስ፤ ሁላችንም «የኛ» እስክንላቸው ድረስ .... መሰራት አለበት። ከዛ በኋላም እንደዛው፤ ከሁኔታው ጋር በሚሄድ መልኩ ጥናትና ምርምሩ ይቀጥላል ማለት ነው።

ከላይ አትኩረንበት ወደ ነበረው፤ «የማይዳሰስ ባህላዊ ቅርስ" ወደ ሆነው፤ እውነትን ወደ አደባባይ የማውጣት ባህልን፤ እንደበተ ርቱዕነትን፤ በራስ የመተማመንና ባህሉንም ከማስተላለፍ አኳያ «የተዋጣ» የተባለለትን፤ «ጥንታዊ ፍትህ አሰጣጥ ስርአት» እንመለስና አሁናዊ ይዞታውን እንመልከት።

ዶናልድ ሌቪን በ«ዋክስ ኤንድ ጎልድ (ሰምና ወርቅ) መጽሐፋቸው «ሙግት በአማራው ማህበረሰብ ውስጥ ያለውን ጉዳት ጠቅሰው አልፈዋል፡፡ ቻይናዊያን ይህንን ባህል አይጠቀሙበትም ነበር፡፡ ወደ ፍርድ ቤት መሄድን እንደጊዜም ሆነ ገንዘብ አባካኝነት ይቆጥሩት ነበር፡፡ በቻይና ባለጉዳዮች በሻይ ቤት ውስጥ ተሰብሰበው በመወያየትና በመደራደር በመካከላቸው ለተፈጠረው ችግር መፍትሄ ይሹ ነበር፡፡» በማለት ማስፈራቸውም ብዙ ጊዜ የሚጠቀስላቸው ሀሳባቸው ነው።

ጄነራል ቨርጂን «እኔ የማውቃት አቢሲኒያ» The Abyssinia I know መጽሐፋቸው በተሟጋቾች መካከል የሚደረገውን ሰርዓት ማራኪ መሆኑን፤ የነበረውን የቃላት አጠቃቀም፣ በተሟጋቾች መካከል የሚደረግ የሰውነት እንቅስቃሴ ሳይቀር እጅግ ውብ እንደነበር መፃፋቸውም በመስኩ አጥኚዎች በኩል ሳይጠቀስ የሚታለፍ አይደለም።

ችግር ባለበት ስፍራ ሁሉ የፍትህና ርትእ ጉዳይ አንገብጋቢ የመሆኑ ጉዳይ የግድ ነው። በመሆኑም የዳኝነት ስርአት ጉዳይ የማይታለፍ ሆኖ ከፊት ድቅን ይላል። በዚህ ጊዜ የተለያዩ አማራጮችን መፈለጉ የማይቀር ይሆናል ማለት ነው።

በዚህ፣ ከዘመናዊው የፍትህ ስርአት ባሻገር አማራጭ ይፈለግ ከተባለ ወደ የትም ሳይሆን የሚኬደው ወደ አገር በቀል እውቀት ያፈራቸው እሴቶቻችን መሆኑ የማይቀር ነው። ይህም የሚወስደን ወደ የማይዳሰስ ባህላዊ ቅርስ ወደ ሆነው ጥንታዊ ፍትህ አሰጣጥ ስርአት ነው። «ለመሆኑ ይህ ስርአት በአሁኑ ሰዓት ነፍሱ አለ?» የሚል ጥያቄ ከተነሳ መልሱ «አዎ፤ አለ»። የመኖሩን ማረጋገጫ እንመልከት።

በሕይወት ስለ መኖሩ ማረጋገጫችን በቅርቡ በማእከላዊ ጎንደር ዞን ጉዳያቸው በፍርድ ቤት ከተያዙ ሰዎች (መዝገቦች) ውስጥ ከ85 በመቶ በላይ አፈፃፀም የተመዘገበው በባህላዊ ፍትህ አሰጣጥ ስርአት አማካኝነት መሆኑን ስንሰማ ነውና፤ ወደ ፊት ከዚህ የበለጠ ይሰራበታል ብለን እንጠብቃለን።

በማጠቃለያችን የአገር በቀል እውቀታችን ወቅታዊ ይዞታ ምን እንደሚመስል በማሳየት መሰናበት ሲሆን፤ የጥንታዊው የፍርድ አሰጣጥ ስርአቱ በተወሰኑ አካባቢዎች እየተሰራበት ይገኛል። በኦሮሚያም ወደ ዘመናዊ አሰራር የተሻገረው ቡሶ ጎኖፋም እንደዚሁ እየተሰራበት ነው። በደቡብ ጎንደር ዞን የሆነውም ከላይ እንዳየነው ነው። በመሆኑም ሌሎችም ከዚህ አፈፃፀም ልምድ ቢወስዱና አገር በቀል እውቀቶቻችንን ብንጠቀምባቸው የተሻለ ይሆናል ተብሎ ይታሰባል።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

# «እርዳታ ማለት የአይጥ ወጥመድ ላይ የሚቀመጥ ፍርፋሪ ማለት ነው»

-ጠ/ሚ ዶክተር አብይ አህመድ

አስናቀ ፀጋዬ

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ለመጀመሪያ ጊዜ ከሁሉም ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች የተውጣጡ ወጣቶችን በጽህፈት ቤታቸው አዳራሽ ተቀብለው ባለፈው ሳምንት አወያይተዋል። ወጣቶቹ በሀገራዊ፣ ቀጣናዊና በራሳቸው ጉዳይ ላይ ላነሷቸው ጥያቄዎችም ማብራሪያና ምላሽ ሰጥተዋል።

ወጣቶቹ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ካነሷቸው ጥያቄዎች መካከል በአማራ ክልል በጦርነቱ ምክንያት የተፈናቀሉ ዜጎችና መልሶ ለማቋቋምና የተቋረጡ የመሰረተ ልማት አውታሮችን ከማሟላት አንፃር ምን ስራዎች እየተሰሩ እንደሆነና ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለወጣቱ የስራ እድል ለመፍጠር ምን አይነት ስራዎች እየተከናወኑ እንደሆነ ይገኙበታል።

በትግራይ ያለውን ድህነት ለማጥፋትና አሁን ላይ በህዝቡ ላይ የሚደርሰው ሰቆቃ እንዲያበቃ ለማድረግ መንግስት ምን እየሰራ እንደሚገኝና ከለውጡ ጋር በተያያዘ የወጣቱ ቀጣይ ሚና ምን መሆን እንዳለበትም ከወጣቶቹ ጥያቄ ቀርቧል።

በሃረሪ ክልል ያለውን የቱሪዝም መሰረተ ልማት ችግር ከመፍታት አንፃር ምን አይነት ስራዎች እየተሰሩ እንዳሉና በከተማዋ የሚታየውን የመጠጥ ውሃ ችግር ለመቅረፍ በመንግስት በኩል ምን እየተሰራ እንደሚገኝም በወጣቶቹ ተጠይቋል።

ሸኔ በኦሮሚያና በሌሎች ብሄር ተወላጆች ላይ እያደረሰ ያለውን ግድያ ለማስቆምና ሸኔ ያለባቸውን አካባቢዎች ለማፅዳት ምን እንደታሰበ ከዚህ አኳያ የወጣቶችስ ሚና ምን መሆን እንዳለበትም ወጣቶቹ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ አንስተዋል። የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ከመፍታት አንፃርም በመንግስት በኩል ምን እየተሰራ እንዳለም ተጠይቋል።

በሱማሌ ክልል ሩዝን በስፋት ለማልማትና የእንስሳት ሀብትን ለማዘምን ምን ታስቧል የሚል ጥያቄም በወጣቶቹ የተነሳ ሲሆን፤ ድሬዳዋን በሚመለከትም የድሬዳዋን ህዝብ ኑሮን ለማሻሻል መንግስት ምን እየሰራ እንደሚገኝ ተጠይቋል።

አዲሱን የደቡብ ምእራብ ክልልን ሀብት በስፋት ጥቅም ላይ ለማዋልና ክልሉንም ለማጠናከር በመንግስት በኩል ምን እንደታሰበ፣ በቤኒሻንጉል ክልል ያለውን የፀጥታ ችግር ለመፍታት መንግስት ምን እየሰራ እንደሚገኝ፣ በክልሉ የተፈናቀሉ ዜጎችን መልሶ በማቋቋም ረገድስ በመንግስት በኩል ምን እንደታቀደም ወጣቶቹ ያነሱት ሌላው ጥያቄ ነው።

የስራ እድል ፈጠራና የወጣቱን ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በመንግስት በኩል ምን አይነት ስራዎች እየተሰሩ እንደሚገኙም ከወጣቶቹ ጥያቄዎች ተነስተዋል። በነዚህና በሌሎች ጥያቄዎች ላይም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ማብራሪያና ምላሽ ሰጥተዋል፤ እንደሚከተለው አቅርበነዋል።

ኢትዮጵያን እናንተ ብቻ ሳትሆኑ እኛም አውቀን አልጨረስናትም። ኢትዮጵያ በርካታ የተፈጥሮ ሀብቶች አሏት ግን አውቀን አልጨረስነውም። የአፍሪካ 50 ከመቶው ተራራ በኢትዮጵያ የሚገኝ ቢሆንም ተራራን ማልማት፣ በተራራ ውስጥ መጓዝና የተራራን ጥቅም ለማወቅ ብዙ መንገድ ይቀረናል። ከዚህ አኳያ ሀገራችንን ለማወቅ ብዙ መጣር አለብን።

በቀጣይ የሚታሰበውም አንድ ወጣት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ካጠናቀቀ በኋላ ወደዩኒቨርሲቲ ከመግባቱ በፊት ለጥቂት ወራት ብሄራዊ አገልግሎት እንዲሰጥ ነው የሚፈለገው። ይህን አገልግሎት ወጣቱ ከአካባቢውና ከክልሉ ውጪ ያለውን ሀገራዊ ሁኔታ ለማየት ይጠቀምበታል። ይህም በፍቃደኝነት ነው የሚሆነው። ነገር ግን ደግሞ ሀገሩን የማያውቅ ወጣት ስራ አይቀጠርም።ለስራ ቅጥር አንዱ መመዘኛም ሀገርን ማወቅ ይሆናል።

ኢትዮጵያ የሆነ ጊዜ ላይ ጠንካራና ሃያል ሀገር ነበረች። ኢትዮጵያ ልክ እንደ ንስር አሞራ ሶስት ነገሮችን አጥታለች። አንዱ ያጣችው ነገር ሰው ነው። ዜጎቿን በፍቅርና በአንድነት ማቆየት አልቻለችም። ያጣቻው አንድነትን ቢሆንም ታዲያ አንድነት ሲባል ግን አንድ



አይነት ማለት አይደለም። በፆታ፣ በቋንቋና በእምነት ልዩነት አለ። ስለሆነም እንደ ንስር አሞራ ዳግም ራስን ለማደስ እንደሀገር አንድ ሀገራዊ ማንነት ይዞ ለመቆም የሚያስችልና የሀገርን ማስጠበቂያ አውድ መመለስ አለበት። ለዚህም የራሱ ሂደት ይጠይቃል። ይህን ካደረግን የውጪ ተፅእኖ ይቀንሳል። ይህ እንዲሆን ደሞ ከአቧራ ፖለቲካ ወደ አሻራ ፖለቲካ መቀየር አለበት።

ሁለተኛው ኢትዮጵያ ያጣችው ነገር የተፈጥሮ ሀብቷን ነው። ተፈጥሮ የሰጣትን አውድ ተገንዝባ መጠበቅ አለመቻል ነው። የተፈጥሮ ሀብቷም ተረስቷል። ሶስተኛው የኢትዮጵያ ሃይልና ጉልበት የነበረውና ሀገሪቱ ያጣችው ነገር ደግሞ ከመሬት ተነስቶ ፈጣሪን ማናናቅና መጥላት ነው። ይህም በመንግስትም በኩል የሚታይ ነው።

ስለሆነም እንደ ንስር አሞራ ዳግም ራስን ለማደስና ወደነበርንበት ለመመለስ በተፈጥሮ ሀብትና በአንድነት ላይ መስራት ፈጣሪን መክዳት ኪሳራ እንጂ ትርፍ እንደሌለው መረዳት ይገባል። እነዚህ ሶስት ጉዳዮችን መመለስ ሲቻል ኢትዮጵያ ወደነባር ከፍታዋ ትመለሳለች። ከዚህ አንፃር እናንተ ወጣቶች ኢትዮጵያ የጎደሏትን ሦስት ነገሮች መመለስ አለባችሁ።

ለዚህም ወደ‌ኋላ መለስ ብሎ የነበሩ ለውጦችን መቃኘት ያስፈልጋል። ለምን በፍጥነት እንደወደቅን ማጤን ይገባል። ምን ብናደርግስ ነው ከውደቀት አገግመን ልንድን የምንችለው የሚለውን ማሰብ ይኖርብናል። ቀደም ሲል ከነበሩት መንግስታት በወታደራዊ ሀይል መምጣት ጥቅም አልባ ስለመሆኑ ትምህርት መውሰድ ይገባናል። ከዚህ አኳያ ቅድሚያ ሰጥተን የሰራነው የዲሞክራሲ ተቋማትን በማጠናከር ነበር። ለዚህም ምርጫ ቦርድን፣ እምባ ጠባቂን፣ ሰብአዊ መብት ኮሚሽንን፣ ፍርድ ቤትን፣ ሲቪክ ማህበራትን የሚያጠናክሩ ህጎች ላይ ተሰርቷል፤ ተቋማቱ ከፖለቲካ ነፃና ገለልተኛ በሆኑ ሰዎች እንዲመሩ ተደርጓል። የሚዲያ ነፃነት እንዲመጣም ተደርጓል።

ከዚህ በኋላ ደግሞ ሕወሓትን ጨምሮ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ከመንግስት ጋር አብረው እንዲሰሩና እንዲቀጥሉ ጥሪ ቀርቦላቸዋል። ምርጫ ካሸነፍን በኋላም ብቻችንን እንምራ አላልንም። ሌሎች ፓርቲዎችም ከኛ ጋር ይሁኑ ብለን መንግስት ይሁኑ ብለናል።

ይህ ብቻ በቂ ስላልነበረ ሶሻል ካፒታል እናጠናክር ብለን አንደኛ ሁለት የነበረውን የኦርቶዶክክስ ሲኖዶስ አንድ አደረግን። ሁለተኛ ሙስሊሙ ውስጥ የነበረውን ኩርፊያና ሌሎች ጥያቄዎችን መለስን። በተመሳሳይ ፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮችን በማወያየት ኢትዮጵያ እንዳትፈርስ ጥረት አድርገናል።

ኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው የፖለቲካ ትርክት ከፋፋይ ስለነበር የሚያሳስብ ነገር ላይ ማተኮር ያስፈልጋል በሚል ሁሉንም የሚያስተሳስርና አንድ የሚያደርግ ብልፅግና ፓርቲ እንዲወለድ ተደርጓል። ሂደቱ ግን ቀላል አልነበረም።

የመደመር፣ የፍቅር፣ የሰላምና የአንድነት ጉዳይ በህፃናት ጭንቅላቶች ውስጥ ተቀርፀዋል። እነሱ ሲያድጉ ቋንቋቸው የሚሆነው መደመር፣ ፍቅር፣ ሰላምና አንድነት ነው።

ዲሞክራሲ ላይ ቢሰራ፣ የሃይማኖት ተቋማት ቢገነቡ፣ ፓርቲዎች አንድ ቢደረጉ ነገሩን ባፋጣኝ መልክ ማስያዝ ስለማይቻል የህግ የበላይነት እንደሚያስፈልግና ለዚህ ደግሞ የህግ አስፈፃሚ አካላት ማለትም መከላከያ፣ የደህንነት ተቋማት እንዲጠናከሩ ተሞክሯል። መከላከያም ሆነ ደህንነት ተቋማት ኢትዮጵያዊ መስለው እንዲገነቡ ያስፈለገበት ዋነኛው ምክንያትም ከዚህ ቀደም የነበረውን ስህተት ላለመድገም ነው።

ተቋማት እንዴት እየተገነቡ እንደሆነ ሳናውቅና በውስጣቸው ሳናልፍ ግን እንዲሁ ስም ከሰጠን መልሰን የነበርንበት ጥፋት ውስጥ ከመግባት ውጪ ጥቅም የለውም። ሀገር እንድታድግ የሚፈልገው ሰው የተጀመረውን ሳያፈርስና ሳያበላሽ ከላዩ ላይ እየገነባ የሚሄድ መሆን አለበት።

ዲሞክራሲ፣ እምነት ተቋማት፣ ፓርቲዎችና የህግ የበላይነት ላይ ቢሰራም ቴክኖሎጂ ከሌለ ዋጋ ስለማይኖረው በእያንዳንዱ መስሪያ ቤት ቴክኖሎጂን ለማረጋገጥ ጥረት ተደርጓል። ቴክኖሎጂን በስርአቱ ውስጥ ለማካተትና ለወጣቱ የሚመጥን ተቋም ለመገንባት ተሞክሯል።

ኢኮኖሚን በሚመለከትም የንግድ ብድር ተኮር የነበረውን የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ባለፉት አራት አመታት የንግድ ብድርን ለማቆም ወስናለች። እስካሁንም ምንም አልተበደረችም። በሌላ በኩል በየቦታው እያረሩ ያሉ ፕሮጀክቶች በፍጥነት እንዲጠናቀቁ ስራዎች ተሰርተዋል። እነዚህም ፕሮጀክቶች እንዲጠናቀቁ የተደረገው የመንግስትን በጀት በአግባቡ በመጠቀምና ከአጋዥ ሰዎች ብር በመሰብሰብና በበጎ ፍቃደኛ ወጣቶች ነው። እነዚህ ሶስት ነገሮች ሳይቋረጡ ባህል ቢሆኑ የሀገሪቱ እድገት ይፋጠናል።

ለውጥ የሚመጣው ደረጃ በደረጃ ነው። ለውጥ ለእኛ ብቻ ሳይሆን ለልጆቻችንም ጭምር ነው። ሆኖም ያንን ለውጥ ማባዛትና ባጠረ ጊዜ ውስጥ ሁሉም ጋር ማየት ያስፈልጋል። በጋራ ተቸግረንና ወስነን ካልሰራን እንዲሁ ለውጥ አይመጣም። በሀገራት ያየነውን ልምድ ወስደን፤ ከመልካም ልምዶቻቸውም ልምድ ቀስመን፤ ከትጋታቸውም ትጋት ወስደን አንድ ሆነን ብንሰራ ኢትዮጵያ የምትቀየር ሀገር መሆኗን ያመላክታል። ለዚህ ደግሞ የተዘጋውን ኢኮኖሚ መከፈት ያስፈልጋል።

እድገትን በሚመለከት ግን እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ሰፊ የወጣት ቁጥር ያላቸው ሀገራት የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር ወጣቱን አንቀሳቅሶ መስራት ከተቻለ እድገትን ማረጋገጥ ይቻላል። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ አጠቃላይ የመንግስት ተቋም ህጎችንና ፖሊሲዎችን ለማሻሻል ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ። ከዚህ አኳያ ቀሪ ችግር የሆኑትን ሌብነትንና እለተኝነትን መዋጋት ያስፈልጋል።

በአረንጓዴ አሻራ 20 ቢሊዮን ታቅዶ 25 ቢሊዮን ችግኝ ተተከለ ሲባል እንደዋዛ የሚታይ አይደለም። በሁሉም ሴክተር ያቀድነውን በዚያ ልክ ማሳካት ከቻልን ስደት ይቀራል፤ ህልመኞችም ከነህልማቸው ጥግ ጥጋቸውን ይይዛሉ፤ ወጣቶች ሀገር ተረካቢዎች፣ የተሻለች ሀገር የተሻለ ምድር መረከብ ይችላሉ።

በሌላ በኩል ፕሮጀክት ላይ በተለይ ደግሞ በታላቁ የህዳሴ ግድብ በያዘው ውሃና በተፈጠሩ ሰባ ደሴቶች ላይ በቀጣይ ስራዎች ሲሰሩ ግደቡ ክልል ሳይሆን ሀገር ይሆናል። በተመሳሳይ በኮይሻ፣ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ላይ ስኳር፣ መንገድና ትምህርት ላይ በጣም ሰፋፊ ስራዎች ተሰርተዋል።

እነዚህንና መሰል የተጀመሩና ስራቸው እየተጠናቀቁ ያሉ ፕሮጀክቶች ሙሉ ፍፃሜያቸውን እንዲያገኙ ከወጣቱና ከሁሉም የህብረተሰብ ክፍል አስተዋፅኦ ይጠበቃል።

በቀጣይ ዓመት በሚጀመረው በእንቁላል፣ ወተት፣ ስጋ፣ ዶሮና ማር ላይ ስራዎች ይሰራሉ። ከዚህ አኳያ በአረንጓዴ አሻራ የመጣውን ድል በዚህ አዲስ አሻራም መድገም አለብን። ለዚህም በየቦታው እምቅ አቅም አለ። የተሰጠንን አውቆ መጠቀም ያስፈልጋል፤ ሰጪውንም ማመስገን ይገባል።

ወጣቶች የምትፈልጉት ነገር ላይ ማተኮር ሲገባችሁ የማትፈልጉት ነገር ላይ ጊዜያችሁን አታባክኑ። የማትፈልጉትን ነገር አእምሯችሁን አታስተምሩት። ለአብነት ድህነት ድህነት... አትበሉ ምክንያቱም አእምሯችሁ ቃሉን ይለማመደውና ጭንቅላታችሁ ደሃ ይሆናል። ደጋግመን ልማትና ብልፅግና ነው ማሰብ ያለብን።

«እርዳታ ማለት የአይጥ ወጥመድ ላይ የሚቀመጥ ፍርፋሪ» ማለት ነው። ስንዴ የሚረዱ ሀገራትም እንደፍርፋሪው ናቸው። ይህም በአባቶቻችን ንፁህ ደም የተከበረውን ነፃነት በስንዴ መሳይ ይሸጣል እንደማለት ነው። ይህንንም በፈጠነ ጊዜ ማድረግና ስንዴን ከራስ አልፎ ወደውጪ መላክ ያስፈልጋል። ለዚህም ወጣቶች ተዘጋጁ።

እነዚህን በአራት አመታት ውስጥ የተከናወኑ ስራዎችን ለማደናቀፍ የውጪ ጠላቶች በከፍተኛ ደረጃ መዋእለ ነዋያቸውን አፍስሰዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ባንዳዎችና ሸኔ ሀገሪቷን ለማፍረስና ስራዎችን ለማደናቀፍ ሰርተዋል። አለም አቀፍ ቀውስ በተለይ ደግሞ ኮቪድ-19ም የራሱን አሉታዊ ተፅእኖ አሳድሯል። ሀገራዊ ፈተናዎች በተለይ ደግሞ አንበጣ፣ ጎርፍ፣ ኮንትሮባንድና ሀሰተኛ ወሬዎችና ጦርነቶች በአራት አመታት ውስጥ ከገጠሙ ፈተናዎች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው።

ወጣቱ የቀደመ ታሪክ የሰማ ነው። ይህንንም ለውጥ ለማምጣት የታገለ ወጣት ነው። ይህ ወጣት በታሪክ አጋጣሚ የራሱ የሆነ ታሪክና ገድል ያለው ነው። ትናንትን የሰማና ነገን ለመስራት የሚነሳሳ ነው። ከዚህ አንፃር ወጣቶች ጊዜያችሁ አላቂ መሆኑን አውቃችሁ መጠቀም አለባችሁ።

ከውጪ ተፅእኖ አንፃር የኢኮኖሚ፣ ዲፕሎማሲ፣ ወታደራዊና የቴክኖሎጂ ተፅእኖ አለ። ከዚህ አንፃር በተለይ ቴክኖሎጂ ላይ ወጣቶች ቴክኖሎጂን የምትወዱና የምትፈጥሩ መሆን አለባችሁ። ዲፕሎማሲም በዚህ ይወሰናል።

ይህን የውጪ ተፅእኖ ለመቋቋም እያንዳንዱ ግለሰብ በሽታን ለመከላከል ኢሚዩኒቲውን ማሳደግ እንዳለበት ሁሉ ሀገርም እንደዛው ነው። ከሀገር የሚጠበቀው መከላከል የሚያስችል አቅም መገንባት ነው። ይህን በደም የተከበረ ሀገር በቴክኖሎጂና በእርዳታ ምክንያት እንዳይፈርስ መከላከል ነው። ይህን ማድረግ ከቻልን የምናስበውን እናሳካለን። በሰላምና በብልፅግና አሸናፊ መሆን አለብን።

ግጭትን በሚመለከት ሊበዛ የቻለው ነገሮች በብዛትና በቶሎ ማወቅ ነው። ተዋንያንና ሁሉ ተንታኝ መሆን መብዛትም ለግጭት መብዛት ምክንያት ነው። የሽማግሌ መጥፋትም ግጭቶችን አባብሷል።

ወጣትና የተማረ የሰው ኃይል እየበዛ በመሆኑ ስራ ላይ ሰፊ ስራ ያስፈልጋል። በነፃ ማገልገል በገበታ ለሀገርና በሌሎች ፕሮጀክቶች ሁሉ በርካታ ሰዎች በስራ ይሳተፋሉ። በበጀትም እንደዚሁ። የግል ሴክተሩንም እያጠናከርን ስራ ማስፋት አለበን። ከዚህ አኳያ ወጣቶች ስራ መናቅ ማቆም ይኖርባችኋል። በየአካባቢያችሁ ያለውን እድል ማየት አለባችሁ። በተናጥል ሳይሆን በጋራ መስራትን አስቡ።

# የምድር በረከት

# ባህላዊ የወርቅ አምራቾችን የሚታደገው የወርቅ ማጠቢያ ማሽን

**ስምስም መንግሥቱ**

ኢትዮጵያ ያላት የማዕድን ሀብት መጠንና በዘርፉ ልማት ለማካሄድ ያለው የተመቻቸ ሁኔታም ተደጋግሞ ይገለጻል፡፡ ለጌጣጌጥ የሚውሉ የከበሩ እንዲሁም የግንባታና የኢንዱስትሪ ግብአት ማዕድናት በተለያዩ ክልሎች በስፋት የሚገኙ ከመሆናቸው በተጨማሪ ለሀገሪቱም ኢኮኖሚ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ናቸው፡፡

ከከበሩ ማእድናት መካከል አንዱ የሆነው የወርቅ ማዕድን አምራች ከሆኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች አንዱ የኦሮሚያ ክልል ነው፤ በክልሉ ሁለቱ የጉጂ ዞኖች፣ ቦረና እና ሶስቱ የወለጋ ዞኖች እንዲሁም ኢሉባቦር የወርቅ ማእድን በስፋት ይገኛል፡፡ ሻኪሶ ለገደንቢ አካባቢ ደግሞ በወርቅ ሀብቱና ምርቱ በስፋት ይታወቃል፡፡ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልልም የወርቅ ማዕድን በስፋት ከሚገኝባቸው ክልሎች አንዱ ነው፡፡ እነዚህ አካባቢዎች በዋናነት ይጠቀሱ እንጂ፣ መጠኑ የተለያየ የወርቅ ማዕድን በመላ ሀገሪቱ ይገኛል፡፡

በእነዚህ ክልሎች የወርቅ ማእድን የማውጣት ስራ እየተካሄደ ሲሆን፣ ከእዚህም አምራቾቹ፣ ክልሎቹ፣ ማእድናቱ የሚገኙባቸው አካባቢዎች ጭምር ተጠቃሚ እየሆኑ ከመሆናቸው በተጨማሪ ማእድኑ ለውጭ ምንዛሬ ግኝት አስተዋጽኦ እያደረገ ነው፡፡

እንደሚታወቀው፤ ኢትዮጵያ በዓለም ገበያ ላይ አቅርባ የውጭ ምንዛሪ ገቢ ከምታገኝባቸው ዋና ዋና የውጭ ምርቶች አንዱ ወርቅ ነው፡፡ በመሆኑም የወርቅ ልማቱ ወርቅ የማንጠር ክህሎትን ባላቸው በባህላዊ ወርቅ አምራቾች እና በኩባንያዎች አማካኝነት እየተመረተ ለብሄራዊ ባንክ እንዲገባ ይደረጋል፡፡

በኩባንያ ደረጃ ወርቅ ኢትዮጵያ ውስጥ ከሚያመርቱ ወይም ከሚያለሙ መካከልም ሜድሮክ ኢትዮጵያ የሚጠቀስ ቢሆንም፣ በልማቱ ከፍተኛውን ድርሻ የያዙት ባህላዊ አምራቾች እንደሆኑ ይገለጻል፡፡ ምንም እንኳን ከወርቅ ልማት የሚገኘው ገቢ በዓለም ገበያ ዋጋ ተለዋዋጭነት የሚወሰን ቢሆንም፣ ኢትዮጵያ ግን ከዘርፉ የምታገኘው ገቢ ካላት እምቅ አቅም ጋር የሚመጣጠን እንዳልሆነ ተደጋግሞ ይነሳል፡፡

ለዚህም እንደ ምክንያት ከሚቀርቡት መካከል የወርቅ ልማቱ ጊዜንና ጉልበትን ቆጣቢ አለመሆኑ፣ በጥራትም አለመመረቱ በአጠቃላይ ልማቱ አለመዘመኑ የሚሉት ይገኙበታል፡፡ ባህላዊ ወርቅ አንጥረኞቹም ቢሆኑ የልፋታቸውን ያህል ዋጋ እንደማያገኙና በዚህም ኑሮአቸው ላይ ለውጥ ማምጣት እንዳልቻሉ ከባለጉዳዩቹ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በአብነትም የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ከሶስት አመት በፊት ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ሸርቆሌ ወረዳ ላይ ተገኝቶ ካሰራጨው ዘገባ ያገኘነውን መረጃ መጥቀስ ይቻላል፡፡ በወቅቱ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር ተብሎ ይጠራ የነበረው ተቋም በክልሉ የወርቅ ልማት ሥራውን ለማዘመን የሚያግዝ በሸርቆሌ ወረዳ ውስጥ የማሽን ተከላ እንዲከናወንና በዚህም ከ50ሺ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር በእቅድ የያዘውን ሥራ በተመለከተ ለመዘገብ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ጣቢያ በስፍራው ተገኝቶ ነበር፡፡

በወቅቱም ጣቢያው ካነጋገራቸው ባህላዊ ወርቅ አምራቾች መካከልም አንዳንዶቹ በሰጡት አስተያየት እንዳሉት፤ የቁፋሮ ሥራውን የሚያከናውኑት በግምት ነው፤ በግምት ቁፋሮ ተካሂዶ አፈሩ ከወጣ በኃላ በውሃ አጥቦ የመለየቱ ሥራ ተከናውኖም ማዕድኑ ሊገኝም ላይገኝ ይችላል፡፡ አልሚው በለስ ከቀናው ተደስቶ ጥሬ ወርቁን ለገበያ አውሎ ገቢ ያገኛል፡፡ ካልቀናውም አዝኖ ሌላ ዕድል ይሞክራል፡፡

አልሚው ማዕድኑን እስኪሚያገኝ ድረስ ጥልቅ ጉድጓድ ውስጥ መዝለቅ ይጠበቅበታል፡፡ በዚህ ወቅት ለመተንፈስ አየር ሊያጥረው ይችላል፡፡ በዚህም ለጤና ችግር እና ለሞት አደጋ የመጋለጥ እድሉ ሰፊ ነው፡፡

ረዘም ያለ ጊዜ ወስዶ ቆፍሮ ያወጣውን አፈር በውሃ በማጠብና በባህላዊ ዕቃ እያጠለለ ወርቁን ከአፈሩ ለመለየት በሚያደርገው ጥረትም እንዲሁ ለጤና ጉዳት ተጋልጦ ጊዜና ጉልበትን በሚወስድ አሰራር ውስጥ ሊያልፍ ይችላል፡፡ በዚህ ድካም ውስጥ አልፎ ያገኘውን ወርቅ ሸጦ የሚያገኘው ገቢም ወርቁን ከመሬት ውስጥ ቆፍሮ ያወጣበትን ጊዜና ጉልበቱንም



**በወጣቶቹ በመሰራት ላይ ያለው የወርቅ ማጠቢያ ማሽን፤**

ያፈሰሰበት እንዲሁም ጤናውን ለአደጋ ያጋለጠበትን ሁኔታ የሚያካክስ አለመሆኑን ብቻ አይደለም አስተያየት ሰጭዎቹ በቁጭት የተናገሩት፡፡ አንዴ ያገኘውን ወርቅ ሸጦ ገቢ ካገኘ በኃላ ለተከታታይ ጊዜ ቁፋሮ ላይ ተሰማርቶ ወርቅ የማያገኝበት አጋጣሚ ሊኖር የሚችል መሆኑን ነው፡፡ ቀደም ሲል ያገኘውን ገቢ ለዕለት መተዳደሪያው ስለሚያውለው ገንዘቡ ያልቃል፡ ፡ ገቢውን ቆጥቦ ኑሮን ለማሻሻል የሚያስችለው ገቢም አይደለም እያገኘ ያለው፡፡ ይህ ደግሞ አምራቾቹ ለውጥ ሳያገኙ በተመሳሳይ ኑሮ ውስጥ እንዲገፉ በማድረጉ ኑሮአቸውን አሰልቺ እንዳደረገው ያስገነዝባል፡፡

ማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር/ የቀድሞውን ማለት ነው/ ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን የሚቆጥብ የወርቅ ማጠቢያ ምሽን በአካባቢያቸው ላይ ተክሎላቸው ከድካማቸው ለማረፍ ተስፋ ቢያደርጉም፣ በተግባር አለማየታቸው አሳዝኗቸዋል፡፡

በቤንሻንጉል ክልል ሸርቆሌ ወረዳ ውስጥ ለመትከል የታቀደው የወርቅ ማጠቢያ ማሽን ፋብሪካ ግንባታ መጓተቱን ነበር በውቀቱ የኢትዮጵያ ቴሌቪዝን ጣቢያ የዘገበው፡፡በወቅቱም በክልሉ 24 የወርቅ ልማት ቦታዎች ተለይተው ለክልሉ ወጣቶች መሰጠታቸውንም ዘገባው አመልክቷል፡፡

ይህን የቆየ መረጃ መነሻ ማድረግ የወደድነው በባህላዊው የወርቅ ልማት ሥራ ላይ የሚስተዋለው ችግር የቆየ መሆኑንና አሰራሩ አለመዘመኑ ጉዳቱ በተለያየ መንገድ የሚጠቀስ መሆኑን ግንዛቤ እንዲኖር ለማስቻል ነው፡፡

ሀገሪቱ ያላት የወርቅ ሀብት መጠንና ሀብቱ የሚገኝባቸው አካባቢዎችና ያላቸው የወርቅ ማእድን መጠንም በሚገባ ተለይቶ እንደማይታወቅ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይህን ውድ ሀብት በሚገባ ለማወቅና በተደራጀ የአሰራር ሥርአት ልማቱ እንዲከናወን ለማድረግ ጥናታዊ ሥራዎች እንደሚያስፈልጉ በተለያዩ ወገኖች ምክረሀሳቦች ይሰጣሉ፡፡

የማዕድን ሚኒስትር ኢንጂነር ታከለ ኡማ በአንድ ወቅት ከፋና ብሮድካስት ጋር በነበራቸው ቆይታ ኢትዮጵያ የወርቅ ሀብት ቢኖራትም፣ እንደ ደቡብ አፍሪካ፣ታንዛኒያ፣ጋና የመሳሰሉ ሀገራት ስሟ በማእድኑ አይጠቀስም፡፡ እነዚህ ሀገራት ይበልጧታል፡፡ በዚህ ረገድ የዘርፉን ችግሮች ለይቶ በመቅረፍ መሥራት እንደሚጠበቅ በመንግሥት ታምኖበት የተለያዩ እርምጃዎች በመወሰድ ላይ መሆናቸውን አስታውቀው ነበር፡፡ ሚኒስትሩ በሶስት አመታት ጊዜ ውስጥም 300 ሺ /ሶስት መቶ ሺ/ ኪሎግራም ወርቅ ለማምረት መታቀዱን ነው የተናገሩት፡፡

ሀብቱ የሚገኝባቸው ክልሎችም የየበኩላቸውን ጥረት ለማድረግ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚህ በኩልም በባህላዊ መንገድ የሚመረተውን የወርቅ ማዕድን ልማት ለማዘመን የኦሮሚያ ክልል ማዕድን ልማት ባለስልጣን እያከናወነ ያለው እንቅስቃሴ ይጠቀሳል፡፡

የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ተስፋዬ መገርሣ ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እንደገለጹት፤ በባህላዊ መንገድ ወርቅ የሚያመርቱ ጉልበታቸውን ከማባከናቸው በተጨማሪ በቁፋሮ ያወጡትን ማዕድን በአግባቡ እያጣሩ አይደለም፡፡ ከአንድ ኪሎ አፈር ውስጥ መቶ በመቶ ማዕድኑን ማውጣት እየተጠበቀባቸው እነሱ ግን አነስተኛ መጠን ያለው ወርቅ ነው የሚያወጡት፡፡ ይሄ ብክነት ነው፡፡

ወርቁን ከአፈር ውስጥ የሚያጣራ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ችግሩን ማስቀረት የሚቻልበትን መንገድ ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡ ይህ ደግሞ መንግስት ስራ ብቻ መሆን የለበትም፤ የግሉም ዘርፍ ቴክኖሎጂውን ለወርቅ አምራች ማህበራት በማቅረብ ማገዝ ይኖርበታል፡፡ አቅርቦቱን ፕሮጀክት ቀርጾ መተግበርም ይቻላል፡፡

እዚህ ላይ ዓለምአቀፍ ድርጅቶችም እንዲተባበሩ ማድረግም ሌላው አማራጭ ነው፡፡በአሁኑ ጊዜም አንድ የካናዳ ድርጅት ወደ ስምንት የወርቅ ማጠቢያ ማሽኖች ለክልሉ በማቅረብ እገዛ አድርጓል ሲሉ ዋና ስራ አስፈጻሚው ያብራራሉ ፡፡

እንደ ኃላፊው ገለጻ፤ እንዲህ ያሉ ማበረታቻዎች አምራቹን ያነቃቃሉ፡፡ አምራቾቹ በቴክኖሎጂ አጠቃቀሙ ላይ ስልጠና ወስደው መጠቀም ከጀመሩና ጥቅሙንም ከተገነዘቡ በኃላ በሂደት በራሳቸው የማጠቢያ ማሽኑን ገዝተው ለመጠቀም እንዲነሳሱ እድል ይፈጥራል፡፡ በዚህ መልኩ አጠናክሮ መቀጠል ከተቻለ ችግሩን በዘላቂነት መፍታት ይቻላል፡፡

እንዲህ ያሉ የመንግሥት እንቅስቃሴዎችን መሠረት በማድረግና ዘርፉ ላይ የሚስተዋለውን ክፍተት በማየት ዘርፉን ለማገዝ፣ ራሳቸውንም በኢኮኖሚ ተጠቃሚ ለማድረግ አለፍ ብለውም ቴክኖሎጂውን በሀገር ውስጥ በመተካት በቴክኖሎጂው ራስን ለመቻል፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለግዥ የሚወጣውን ወጪ ለማስቀረት የወርቅ ማጠቢያ ማሽን በሀገር ውስጥ ለመተካት በእንቅስቃሴ ላይ የሚገኙ ወጣቶችንም በሀገር ውስጥ ማግኘት ተችሏል፡፡

የወርቅ ማጠቢያ ማሽን በመፍጠርና ወደምርትም በማስገባት ተጠቃሚው ዘንድ ተደራሽ ለማድረግ በእንቅስቃሴ ላይ የሚገኙት ወጣቶች አባስ ሲራጅ እና ቢቂላ ዮሐንስ ይባላሉ፡፡ ወጣቶቹ የማጠቢያ ማሽኑን በቡራዩ ከተማ ውስጥ ነው እየሰሩ የሚገኙት፡፡ጓደኛሞቹ ለተወሰነ ጊዜ ለብቻቸው ከሰሩ በኃላ ሁለት ልጆች ቀጥረው አራት ሆነው በመሥራት ላይ ይገኛሉ፡፡

ወጣት አባስ ስለወርቅ ማጠቢያ መሣሪያ(ማሽን) ሥራውና ለፈጠራ ሥራው የተነሳሱበትን አጋጣሚ አስመልክቶ እንዳጫወተኝ፤ ወጣቶቹ ሌላው ዓለም ጉልበቱንና ጊዜውን በመቆጠብ የወርቅ ልማትን እንዴት እንደሚያከናውን በውጭ የቴሌቪዥን ጣቢያ ላይ ተመልክተዋል፤ ይህ «ናሽናል ጆግራፊ»በሚል ዝግጅት ላይ በካናዳ አንድ የወርቅ ማጠቢያ ማሽን ሥራ ትኩረታቸውን ይስበቸዋል፤ ማሽኑ በፋብሪካ ውስጥ ተመርቶ እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል ይከታተላሉ፡፡

በሀገራቸው ደግሞ ባህላዊ የወርቅ አምራች ወርቅ ለማልማት የሚደርስባቸውን ስቃይ በመገናኛ ብዙሃን ሲቀርብ ብቻ ሳይሆን ልማቱ በሚከናወንበት ቦታም የማየት ዕድሉን አግኝተው ለመገንዘብ ችለዋል፡፡

አምራቾቹ የወርቅ ማጠቢያውን በግዥ ከውጭ አስመጥተው ለመጠቀም አቅሙ እንደማይፈቅድላቸውም ከገበያው ተገንዝበዋል፡፡ ዋጋው የመንግሥትንም የመግዛት አቅም የሚፈታተን ነው፡፡ አነስተኛ የሚባለው ዋጋ ሁለት መቶ ሺ ዶላር እንደሆነም መረጃ ሰብስበዋል።

ወጣቶቹ ይህን ሁሉ ግምት ውስጥ ያስገባ ውሳኔ ላይ በመድረስ ነው ወደ ሥራ ለመግባት የተነሳሱት። በአጋጣሚ ደግሞ ሁለቱም የቴክኒክና ሙያ ሙሩቅ በመሆናቸው ወደሥራው ለመግባት አልተቸገሩም፡፡

ጓደኛው ቢቂላ በኢትዮጵያ ብረታብረት ኢኒጂነሪንግ ኮርፖሬሽን (ሜቴክ) ውስጥ የመሥራት ዕድል አግኝቷል። ሁለቱም ሙያቸውን መሠረት አድርገው በካናዳ በባለሙያዎች የተሰራውን አስመስለው መሥራቱን ተያያዙት፡፡ ማሽኑን በመስራት ውስጥ አራት አመታትን አስቆጥረዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥም ሰባት የወርቅ ማጠቢያ ማሽኖች ሰርተው ለተጠቃሚው ተደራሽ አድርገዋል፡፡

ሞዴል ያደረጉትን የካናዳን የወርቅ ማጠቢያ ማሽን ሥራ አሁንም ክትትል በማድረግ በየጊዜው ካለው ለውጥ ጋር በመራመድ ሥራቸውን እያሻሻሉ እያቀረቡ ናቸው፡፡ በአሁኑ ጊዜም ማሽኑ በመቆጣጠሪያ (በንዝረት) ኃይል እንዲንቀሳቀስ በማድረግ ለውጥ አምጥተውበታል፡፡

አሁን ደግሞ በካናዳ ጥቅም ላይ እየዋለ ያለውን የ2022 ሞዴል የወርቅ ማጠቢያ ማሽን በሀገር ውስጥ ለማምረት እየሰሩ ናቸው፡፡ ማሽኑን ሲሰሩ ዲናሞ የሚባለው ግብአት ካልሆነ በስተቀር ሌሎች ግብአቶች ከሀገር ውስጥ ምርት ነው የተጠቀሙት፡፡ አብዛኛው ግብአትም ብረት ነክ ነው፡፡

አንድ የወርቅ ማጠቢያ ማሽን ሰርቶ ለማውጣት እስከ አንድ ነጥብ ሁለት ሚሊየን ብር ወጭ ይጠይቃል፡ ፡ ስራው ከ20 እስከ 30 ቀናትም ይወስዳል፡፡ የማሽኑ የአገልግሎት ዘመንም ከ20 አመት በላይ እንዲሆን ተደርጎ ነው የተሰራው፡፡

ማሽኑ በአጭር ጊዜ ውስጥ እስከ አንድ መቶ ቶን የሚደርስ አፈር በማጠብ ወርቁን የመለየት ሥራ የማከናወን አቅም አለው፡፡ በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚያከናውነውን ሥራ በጉልበት ሰራተኛ ማከናወን ቢፈለግ አስርና ከዚያ በላይ ሰዎችን ይፈልጋል፡፡ ማሽኑ ከቦታ ቦታ በማንቀሳቀስ እንዲሰራ ተደርጎ የተሰራም ነው፡፡

የወርቅ ማጠቢያ ማሽን ፈጣሪዎቹ ወጣቶች በአሶሳና ሻኪሶ በወርቅ ልማት ላይ ለተሰማሩ አምራቾች በሽያጭ ማቅረባቸውንም የሚናገረው ወጣት አባስ፣ ማሽኑን ለሚገዛቸው በቦታው ድረስ በመገኘት ስለአጠቃቀሙ ስልጠና እንደሚሰጡም ገልጾልኛል፡፡

ወጣት አባስ እንደተናገረው፤ የማሽኑን ሥራ በራሳቸው ወጭ ሰርተው ገበያ ላይ በማዋል አለማምደው ተቀባይነት በማግኘታቸው በአሁኑ ጊዜ በትእዛዝ የሚያሰራ ደንበኛ ማግኘት ችለዋል፡፡ በማህበር የተደራጁ ወርቅ አምራቾችም ጥያቄ ማቅረብ ጀምረዋል፡፡ከጋምቤላ ክልልም ጥያቄ ቀርቦላቸዋል፡፡

የማሽኑ የፈጠራ ሥራ ባለቤትነት ማረጋገጫ እውቅና (ፓተንት ራይት) ለማግኘት በሂደት ላይ ናቸው፡፡ ሥራቸውን የሚያከናውኑበት የቡራዩ ከተማ አስተዳደር እያበረታታቸውና የመስሪያ ቦታም ሊሰጣቸው መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የማዕድን ሚኒስትሩ ታከለ ኡማም በሥራ ቦታቸው ተገኝተው እንዳበረታቷቸውም ነው ወጣት አባስ የነገረኝ፡፡ ብረቶችን ለማጠፍና ለመቁረጥ የሚያገለግል ቶርኖ የሚባል ለሥራቸው የሚያግዛቸው ማሽን ሊዝ ፋይናንሲንግ በሚባል የብድር አገልግሎት ከልማት ባንክ የሚያገኙበትን ሁኔታ ለማመቻቸትም እየሰሩ መሆናቸውን ይገልጻል፡፡ ብድሩ ከተመቻቸላቸው እስከ ዛሬ ለቶርኖማሽን ኪራይ የሚያወጡትን ወጭ እንደሚያስቀርላቸውና ጊዜም እንደሚቆጥብላቸው ተናግሯል፡፡

እኛም በወጣቶቹ የተጀመረው ባህላዊ የወርቅ አመራረት ዘዴን የማዘመን ጥረት ሊበረታታ ይገባል እንላለን፡፡

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## የሕይወት ቀለሞች

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ዘመኔን የጨረስኩት ከእናቴ ጋር እየተኛሁ ነው። አድጌና ትዳር ይዤ እንኳን ከሚስቴ ቀጥሎ ከእናቴ ጋር የምተኛ ነኝ። አንድ እህት አለችኝ..ሽንታም እህት። ለእናቴም አንድ ለእህቴም አንድ ስለሆንኩ እናትና እህቴ እኔን መሀል አድርገው ነው የሚተኙት። እህቴ ሽንታም ናት..አልጋ ላይ ሳትሸና ከእንቅልፏ የተነሳችበት ቀን የላትም። እኔም ሆንኩ እናቴ በእህቴ ሽንት ሳንበሰብስ ያሳለፍነው ሌሊት የለም። አልጋው መሀል ላይ ዛሬም ድረስ የማይረሳኝ በእህቴ ሽንት ማዲያት ያበጀ..ማዲያት ብቻ አይደለም የተቦተረፈ ፍራሽ አለ። እናቴ ፍራሹን ከእህቴ ሽንት ለመከላከል ያላደረገችው ጥረት አልነበረም። ወፍራም ጨርቅ፣ ውሀ የማያስገባ ነገር፣ ርጥበት የሚከላከል ላስቲክ በዚህ ሁሉ ውስጥ አልፎ ግን የእህቴ ሽንት ሁላችንንም ያዳርሰናል። በልጅነቴ እናቴ ሞክራ ያቃተችው የእህቴን ሽንት መቆጣጠር ይመስለኛል። አንዳንድ ጊዜ ጎርፍ የምትሸና ይመስለኛል..።

ጠዋት ከእንቅልፌ የምነቃው በእህቴ ሽንት ግማሽ ጎኔ እርሶ ነው። በእኛ ቤት የእህቴ አለመሸናት እንደ ተዐምር የሚታይ ነበር። ለሽንታሟ እህቴ ብቻ አይደለም ለእኔም ሆነ ለእናቴ የእህቴ ያለሽንት ተኝቶ መንቃት አዲስ ነገራችን ነበር። ግን እህቴ ሳትሸና የነቃችበት ጠዋት የላትም። እናቴ እህቴ ሳትሸና እንድትነቃ የማታደርገው አልነበረም። ማታ ውሃ አትጠጪ ሽንትሽ ይመጣል ሳትላት ቀርታ አታውቅም። በጊዜ ተኝታ ከሆነ ቀስቅሳ ሽንቷን አሸንታ ታስተኛታለች። በዚህ ሁሉ ስጋትና ቁጥጥር ውስጥ ነበር እህቴ ሽንቷን የምትለቅብን።

እናቴ እህቴን ስትሰድባትም ሆነ ስታመናጭቃት ሰምቼ አላውቅም። ሁሌ እንደሸናችብን ነው..ሁሌ እንዳቆሸሸችን ነው። ግን እናቴ ከአፏ ክፉ ሲወጣ አይቻት አላውቅም። ክፉ ብቻ አይደለም በእህቴ ላይ ፊቷን ስታቀጭምባት ተመልክቻት አላውቅም። ‹ይይ እንዳው! በቃ እንዲህ ብቻ ነው የምትለው። የእናቴ ጸዐዳ ፊት እህቴን ያሞላቀቃት..የልብ ልብ የሰጣት ይመስለኛል.. አይመስለኝምም።

እውነት ለመናገር በዛ ጠዋት እኔም ሆንኩ እናቴ ከእርጥበት በጸዳ እንቅልፍ በቀር አዲስ ነገር አልነበረንም። ግን ተሳክቶልን አያውቅም..ጠዋት በጣም ጠዋት የእህቴን አልጋ ላይ የመሽናት መርዶ ከእናታችን ነው የምንሰማው። እናቴ ምን እንደምታስብ አላውቅም እንቅልፍ የላትም.. አሁን አሁን እጇን ወደ እህቴ መቀመጫ እየሰደደች ፍራሹን ስትፈትሽ እታዘባታለሁ። ገና ሳይነጋ..ገና ለማኝ ሳይጸዳዳ በውርጩ እናቴ ‹ይይ እንዳው! ስትል በእንቅልፍ ልቤ እሰማታለሁ። ያኔ የእህቴን የመሽናት መርዶ፣ የእኔንም መርጠብ አውቀዋለሁ።

ለመኖር ግድ አልነበረኝም፣ በዙሪያዬ ላሉት ነፍሶች የምንበረከክ አልነበርኩም። አይደለም ሽንት ቀርቶ አይነ ምድር ታቅፌ ዓለምን ብዞር እንኳን ግድ የሚሰጠኝ አልነበረኝም። ጠዋት ከእንቅልፌ እንደተነሳሁ ቁርሴን በልቼ ማታ እህቴ በሸናችብኝ ገላና ጥብቆ ትምህርት ቤት እሄዳለሁ። ግዴለሽ መሆኔ የአንዳንድ ነውረኛ ነፍሶች ርግማን እንዳይሰማኝ ቢያደርገኝም ከቅጣትና ከመገፋት ግን አላዳነኝም ነበር። በተለይ ሰኞ ሲሆን ተማሪዎችም መምህራንም ነበር በአዲስት ድህ ነፍሴ ላይ የሚጫወቱት። ሰኞ ሆኖ ሰልፍ ላይ ተማሪ ፊት ያልወጣሁበት ጊዜ የለም። ክፍል ውስጥ በሳይንስ አስተማሪያችን ጆሮ ያልያዝኩበት ጊዜ የለም። በእኔ ምክንያት ብቻ እናቴ በአመት ውስጥ እጅግ ለበረከተ ጊዜ ትምህርት ቤት ተጠርታለች። ሰልፍ ላይ ከዚያም ከዚም እየተጠቋቆሙብኝ ብዙ ፊቶች ይሳለቁብኝ ነበር። ትምህርት ቤታችን ውስጥ እናቴ ካወጣችልኝ ስሜ በላይ ሽንታሙ ተማሪ ሆነ ስሜ። ግን ልበ ሙሉ ነበርኩ። በዛ ሁሉ ወንበዴ ተማሪ ተከብቤ፣ በዛ ሁሉ ነገን በማያስተውሉ መምህራን መሀል ቆሜ ጀብደኛ ነበርኩ። በዛ ጠዋት..በዛ ልጅነቴ ውስጥ የእህቴን ነውር እኔ ነበርኩ የምወስደው። በእህቴ ሀጢአት እኔ ነበርኩ የምገረፈው። የእኩይ ነፍሷ ማረፊያ ነፍሴ ነበረች።

ሰኞን አልወዳትም..ዛሬም ድረስ እጠላታለሁ።

በነጋታው ያው ነኝ.እህቴ ሳትሸናብኝ፣ ዝንቦች ሳይወሩኝ በተፈጥሮ ጠረኔ ትምህርት ቤት ሄጄ አላውቅም። የዛ ሁሉ ተማሪ ነቀራ፣ የነዛ ሁሉ ጓደኞቼ አሽሙር ዘልቆ አይሰማኝም ነበር። አንዳንዴ እኔን በሚያበሽቁኝ ተማሪዎች መሀል ራሴን እየሳኩ አገኘዋለሁ። ብዙ ጊዜ ሽንታሙ ተማሪ እያሉኝ ከሚያበሽቁኝ ተማሪዎች ጋር ወዳጅ ነበርኩ። ኳስ በቡድን እንጫወታለን። ብይ፣ አባሮሽ ሌሎችንም ጨዋታዎች እንጫወት ነበር። በዚያ ሁሉ አብሮነታችን ውስጥ እኔን ለማናደድ፣ እኔን ለማስኮረፍ፣ እኔን ለማስለቀስ የማይፈነቅሉት ድንጋይ አልነበረም ግን በነጋታው አብሬአቸው እስቃለሁ። የሆነ ጊዜ ነውሬን ሰለቹት መሰለኝ..ክብረ አብ ሲሉ እናቴ ባወጣችልኝ ስሜ ይጠሩኝ ጀመር። ሰው አብሮ ካረከሰ በስተቀር እኩዮችን የሚያሸንፍበት አቅም ያጣል ብዬ አላስብም። በልጅነቴ እነዛን በእድሜ የሚበልጡኝን፣ እነዛን በወንድሞቻቸው የሚመኩትን ጓደኞቼን ያሸነፍኩት በመተው ነው እላለሁ። በልጅነቴ እነዛን እልኸኞች፣ እነዛን ትዕቢተኞች፣ እነዛን ጥጋበኞች ዝም ያሰኘሁት በሳቄ ነው እላለሁ። እንጂማ ምን ነበረኝ..ለራሴ የሴት ልጅ።

ቤት ስደርስ እናቴ ገላዬን ታጥበኛለች ግን ማታ በእህቴ ሽንት ሳላድፍ ቀርቼ አላውቅም። ጠዋት የታጠበ ገላዬ፣ በቫዝሊንና እናቴ በአመት አንድ ጊዜ በምታወጣው ሽቶዋ የጠረነ ገላዬ በእህቴ ሽንት ጨቅይቶ አገኘዋለሁ። አብሮ የእናቴ ‹አይይ እንዳው! ይሰማኛል። ቀዝቃዛ ውሃ አልወድም..ቀዝቃዛ ውሀ ከሚነካኝ እድሜ ልክ ሰውነቴን ባልታጠብ የምመርጥ ልጅ ነኝ። ፋሲካ ሲሆን ወይም ደግሞ ራት ሳልበላ የተኛሁ ቀን እናቴ ከእንቅልፌ የምታባንነኝ ቀዝቃዛ ውሃ ፊቴ ላይ በመርጨት ነው። ያኔ አኩርፌ ራት አልበላም ብዬ በግድ አባብላኝ ነበር የምትታረቀኝ። ቀዝቃዛ ውሃ አልወድም። እናቴ እኔን ገላዬን አጥባ ትምህርት ቤት ለመላክ ውሃ ለማሞቅ በጠዋት ትነሳለች። ውሃው እስኪሞቅ ሰዓት ስለሚረፍድ ሳልታጠብ ትምህርት ቤት እሄዳለሁ። ጠዋት በሞቀልኝ ውሃ ከሰዓት ከትምህርት ቤት መልስ እታጠባለሁ። አንድም ቀን ጠዋት ሰውነቴን ታጥቤ አላውቅም..እናቴ ጠዋት ተነስታ ውሃ ብታሞቅልኝም ሰዓቱ ስለሚረፍድ አልታጠብም..ከምታጠብ ይልቅ አለመታጠቤ ነበር የሚያስደስተኝ..ሙቅ ውሃውም ስለሚቀዘቅዘኝ።

በእህቴ ሽንት ስታጠብ ያደኩ ልጅ ነኝ። እህቴ ሳትሸናብኝ፣ ዝንቦች ሳይወሩኝ ተማሪ ፊት ሳልቆም የቀረሁበት ጊዜ የለም። ከእርጥበት የጸዳ ማለዳ፣ ከነቀፋ የራቀ ጠዋት ብርቄ ነበር። አንድ ጠዋት እህቴን ተቀየምኳት..በልደቴ ዋዜማ እህቴ እንዳትሸናብኝ ያላደረኩት ጥረት አልነበረም። ነግቶ በልደቴ ቀን አዲስ ልብስና ጫማዬን እስክለብስ ቸኩዬ ነበር። ማታ በእኔ ምኞትና ማባበል ይሆን ይመስል ዛሬ እንዳትሸኚብኝ ስል እህቴን በብዙ ለመንኳት። እየሰጋሁ በእናቴና በእህቴ መሀል ተኛሁ። ስለልደቴና ስለምለብሰው አዲስ ልብስና ጫማ እያለምኩ ነበር። ጠዋት በጣም ጠዋት እናቴን ‹አይይ እንዳው! ስትል ሰማኋት። እህቴ እንደሸናችብኝ አመንኩ። ዘመኗን ስትሸናብኝ ያልተቀየምኳትን እህቴን ያን ቀን ተቀየምኳት። አዲስ ልብስና ጫማዬን በእህቴ ሽንት ባደፈ ገላዬ መልበስ ግድ ሆነብኝ።

ቀኑ ቅዳሜ ነበር.. እናቴ በልደቴ ቀን ጠዋት ለእኔ ውሃ ልታሞቅ የተነሳችበት ቅዳሜ። ያን ቀን እናቴንም ሆነ ሙቅ ውሃውን የማመልጥበት ምንም አጋጣሚ አልነበረም። በእለተ ቅዳሜ የሚረፍድ ቀን አልነበረኝም በእናቴ ሙቅ ውሃ ሰውነቴን ታጥቤ አዲስ ልብስና ጫማዬን መልበስ እጣ ፈንታዬ ሆነ። ከሁሉም ቀድማ እንኳን ተወለድክ ስትል ጉንጩን የሳመችኝ ሽንታሟ እህቴ ነበረች።

# ዓለም አቀፍ

## ባይደን በሚሊዮኖች ለሚቆጠሩ ተማሪዎች የ10 ሺህ ዶላር እዳ ሰረዙ

የአሜሪካው ፕሬዝዳንት ጆ ባይደን በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ተማሪዎችን የትምህርት ቤት እዳ እንደሚሰርዙ ተገለጸ። ከፌደራል መንግሥቱ የተመደበላቸውን ወደ 10 ሺህ ዶላር የሚጠጋ እዳ ነው የሚሰርዙት። በዚህ እዳ ስረዛ የሚካተቱት በዓመት ከ125 ሺ. በላይ ገቢ የሚያገኙ አሜሪካውያን ናቸው።

ከፍተኛ የገንዘብ ድጎማ ለሚያስፈልጋቸው ተማሪዎች በተዘጋጀ ፕሮግራም ሥር ላሉ ተማሪዎች ደግሞ 20 ሺህ ዶላር እዳ ይሰረዛል። “ከዚህ በኋላ የተማሪ እዳ ሸክም አይሆንባችሁም” ብለዋል ባይደን። ወደ 43 ሚሊዮን የሚጠጉ አሜሪካውያን 1.6 ትሪሊዮን ዶላር የተማሪ እዳ አለባቸው። ከእነዚህ መካከል አንድ አምስተኛው ከ10 ሺህ ዶላር በላይ እዳ ነው ያለባቸው።

በ2020 አጋማሽ በጊዜያዊነት ቆሞ የነበረው የእዳ ክፍያ እስከዚህ ዓመት ማገባደጃ እንደሚቆይ ተገልጿል። ባይደን የእዳ ስረዛ ውሳኔያቸው አነስተኛና መካከለኛ ገቢ ላላቸው “የእፎይታ ጊዜ” የሚሰጥ እንደሆነ ተናግረዋል። “ጫናው ከፍተኛ ስለሆነ ከተመረቃችሁ በኋላ የመካከለኛ መደብ ኑሮ ለማግኘት ትቸገራላችሁ። በአንድ ወቅት የኮሌጅ ዲግሪ ያለው ሰው ኑሮው ከመካከለኛው መደብ ይመደብ ነበር” ብለዋል።



ባይደን እዚህ ውሳኔ ላይ የደረሱት ተራማጅ ዴሞክራቶች ያሳደሩትን ጫና ተከትሎ ዋይት ሀውስ ውስጥ ስለ እዳ ስረዛ ከፍተኛ ክርክር ከተደረገ በኋላ ነው። እዳ እንዲሰረዝ ከፍተኛ ጫና ካሳደሩ መካከል ሴናተሮቹ ኤልዛቤት ዋረን እና ቻክ ሹመር ይገኙበታል። ዕቅዳቸው ከእያንዳንዱ ባለ እዳ 50 ሺህ ዶላር ማስቀነስ ነበር። አሁን የተላለፈው ውሳኔ ግን ከእያንዳንዱ ባለ እዳ አንድ ጊዜ 10 ሺህ ዶላር የሚቀነስ ነው።

ይህም መንግሥትን 300 ቢሊዮን ዶላር እንደሚያስ ወጣው ይገመታል። ባይደን ውሳኔው “የአገሪቱን ምጣኔ ሃብት ያማከለ ነው” ሲሉ ተከራክረዋል። “ሠርቶ አደር አሜሪካውያንን በመርዳቱ አልጸጸትም። ከፍተኛ ገቢ የሚያገኙ ዜጎች የዚህ እዳ ስረዛ ተጠቃሚ አይሆኑም” በማለትም አክለዋል።

ሪፐብሊካኖችና ለዘብተኛ ዴሞክራቶች የእዳ ስረዛው በአሜሪካውያን ኪስ ተጨማሪ ገንዘብ በማስገባት የኑሮ ውድነትን ያባብሳል ሲሉ ተደምጠዋል። ሪፐብሊካኑ ኬቨን ማካርቲ “ለባይደን የእዳ ስረዛ ገንዘብ የሚመጣው ከየት ነው? ብላችሁ ብትጠይቁ፣ መልሱ የተማሪ እዳቸውን ከከፈሉ ዜጎች ነው። እነዚህ ትጉህ አሜሪካውያን የተማሪ እዳ የከፈሉ ወይም ከመጀመሪያውም ገንዘብ ያልወሰዱ ናቸው። ታዲያ ለምን በእዳ ስረዛ ስም ገንዘባቸው ይወሰዳል?” ሲሉ ተችተዋል።

በሌላ በኩል ዴሞክራቶች እንደሚሉት፣ የእዳ ስረዛው በዘር ምክንያት የሚፈጠረውን የገቢ አለመመጣጠን የሚያጠብ ነው ብለው ተከራክረዋል። በብዛት ከፌደራል መንግሥቱ ገንዘብ የሚበደሩት ጥቁር አሜሪካውያን ተማሪዎች ናቸው። ዲግሪ ሲማሩ ለአራት ዓመታት ከመንግሥት የተበደሩት ገንዘብ ወደ 25 ሺ. ዶላር እዳ ይሆናል። ይህም ከነጭ አሜሪካውያን ተማሪዎች የበለጠ እንደሆነ ቢቢሲ ዘግቧል።

## ጀርመን የኃይል ቁጠባ ዕቅድን አጸደቀች

ጀርመን በጋዝ አጠቃቀም ላይ ገደብ የሚጥለውን የኃይል ቁጠባ ዕቅድ ማጽደቋን አስታወቀች። የፀደቀው የኃይል ቁጠባ ዕቅድ ቢሮዎች እና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚጠቀሙትን የሙቀት መጠን ከ19 እስከ 20 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ባለው እንዲሆን የሚገድብ ነው ተብሏል፡፡

ከትናንት ወዲያ የጀርመን ካቢኔ አባላት ከተሰበሰቡ በኋላ የአገሪቷ የኢኮኖሚ ሚኒስትር ሮበርት ሀቤክ በበርሊን መግለጫ ሰጥተዋል፡ ፡ ሮበርት ሀቤክ በሰጡት መግለጫ የጀርመን መንግስት በአገሪቷ በሚኖረው ቀጣይ የሙቀት ወቅት የጋዝ አጠቃቀምን ለመቀነስ ይረዳው ዘንድ የተለያዩ እርምጃዎችን መውሰድ የሚያስችሉ ጥቅል ዕቅዶች ማጽደቁን ተናግረዋል፡፡

በጸደቀው ዕቅድ መሠረትም የምሽት የውጭ ማስታወቂያ ሰሌዳዎች ፣ የመጋዘን በረንዳ መብራቶች በየቀኑ ከምሽቱ 4 ሰዓት ጀምሮ እስከ ንጋት 12 ሰዓት ድረስ ለስምንት ሰዓታት ጠፍተው እንዲቆዩ ተወስኗል ብለዋል፡፡

ውሳኔው ከፈረንጆቹ መስከረም 1 ቀን ጀምሮ ቀስ በቀስ እስከ ጥቅምት ባለው ጊዜ እንደሚተገበር ተነግሯል፡፡

በጸደቀው ዕቅድ መሠረት ጀርመናውያን የጋዝ አጠቃቀማቸውን ከ2 እስከ 2 ነጥብ 5 በመቶ ይቀንሳሉ ነው የተባለው፡፡



የትግበራ እርምጃው እንደ ጤና ተቋማት እና ሆስፒታል ያሉ የማኅበረሰብ አገልግሎት ሠጪ ተቋማትን እንደማይመለከትም አር ቲ መዘገቡን ኤፍቢሲ ዘግቧል፡፡

## ግልፅ የጨረታ ማስታወቂያ

በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በጅማ ዞን የሠቃ ጨቆርሳ ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት በ2015 ዓ.ም የበጀት ዓመት በወረዳው ውስጥ ቀበሌዎችን የሚያገናኙ የገጠር መንገድ ጥገና በማስፈለጋቸው አስተማማኝ የቴክኒክ ብቃት ያላቸው እና ከፍተኛ የሥራ አፈፃፀም ውጤት ማስገኘት የሚችሉ የተለያዩ አይነት ለመንገድ ስራ አገልግሎት የሚውሉ ማሽኖችን ኪራይ በሰዓት በግልፅ ጨረታ ሕጋዊ የሆኑ ድርጅቶችን አወዳድሮ ለማሰራት ይፈልጋል፡፡

በዚሁ መሰረት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ በመንገድ ስራ ዘርፍ የተሰማሩ ድርጅቶችን በጨረታው እንዲሳተፉ እንጋብዛለን ::

**ተሳታፊዎች**

1. ህጋዊ የንግድ ፍቃድ ያላቸው የንግድ ፍቃዳቸውን ያሳደሱ የአመቱን ግብር የከፈሉና ዋናና ቅጂ መረጃ አያይዘው ማቅረብ የሚችሉ፡፡
2. ተወዳዳሪዎች በአቅራቢዎች ዝርዝር ላይ የተመዘገቡበትን መረጃ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
3. ተወዳዳሪዎች ተጨማሪ እሴት ታክስ (ቫት) ተመዝጋቢ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ መረጃ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
4. የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ በተመሰከረ ቼክ CPO 5000.00 ( አምስት ሺህ ብር ) በታሸገ ፖስታ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
5. በጨረታ የሚሳተፉ ተወዳዳሪዎች ከሙስናና ከብዝበዛ ድርጊት የጸዱ መሆን አለባቸው::
6. ጠቅላላ ተወዳዳሪዎች በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስትና የፌዴራል መንግስት የተደነገገውን የግዥ ሕግ የሚያከብሩ መሆን አለባቸው::
7. መልካም የሥራ ልምድና መልካም የሥራ አፈፃፀም ማቅረብ የሚችሉ፡፡
8. ተወዳዳሪዎች ጨረታውን ለማሰናከል ከሞከሩ ከጨረታው ውጭ ይሆናሉ ለወደፊትም በሠቃ ጨቆርሳ ወረዳ በሚካሄደው በመንግስት የግዥ ጨረታ አይሳተፉም፡፡ ለጨረታ ማስከበሪያ ያስያዙት ገንዘብም አይመለስም፡፡
9.በኢትዮጵያ ደረጃ መዳቢዎች የተረጋገጠ ማሽኖች ስለመሆናቸው ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችል::
10. ተወዳዳሪዎች የጨረታ ሰነድ ከተከፈተ በኋላ በሰነዱ ላይ ባቀረቡት የመወዳደሪያ ሀሳብ ላይ ለውጥ/ማሻሻያ ማድረግ ወይም ከጨረታ መውጣት አይችሉም ::
11. ተወዳዳሪዎች በጨረታው ላይ መግለጫ ወይም የማሻሻያ ጥያቄ ካላቸው በተመዘገቡ በአምስት ቀን (5) ውስጥ ማቅረብ ይችላሉ፡፡
12. ተወዳዳሪዎች ባቀረቡት መወዳደሪያ ሰነድ ላይ ስም ፣ ፊርማ ፣ የድርጅቱ ማህተም እና አድራሻ መጥቀስ አለባቸው ::
13. ተወዳዳሪዎች በጨረታው አካሄድ ቅሬታ ካላቸው ለሚመለከተው ክፍል ማቅረብ አለባቸው፡፡
14. የጨረታውን ሰነድ በሠቃ ጨቆርሳ ወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ቁጥር 7 የማይመለስ 200 (ሁለት መቶ ብር ) በመክፈል መግዛት ይችላሉ፡፡
15. ይህ ጨረታ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ20 (ሃያ) ተከታታይ የስራ ቀናት የሰነድ ሽያጭ ይከናወናል::
16. የጨረታው ሰነድ አቅራቢ ድርጅቶች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በ21ኛው የስራ ቀን ጠዋት 3:00 ሰዓት ታሽጎ 4:00 ሰዓት ላይ ይከፈታል ::
17. የተሰረዘ፣ የተደለዘ የተፋፋቀ ወይም በግልፅ የማይነበብ የጨረታ ሰነድ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
18. ግዥ የሚፈጽመው አካል ጨረታውን በከፊልም ሆነ በጥቅል መሰረዝ ይችላል፡፡

**በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በጅማ ዞን የሠቃ**
**ጨቆርሳ ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት**

## ግልፅ የጨረታ ማስታወቂያ

በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በጅማ ዞን የሠቃ ጨቆርሳ ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት በ 2015 ዓ.ም በወረዳው ውስጥ ላሉ ባለበጀት መስሪያ ቤቶች የሚያገለግሉ የጥራት ደረጃቸው በኢትዮጵያ ደረጃ መዳቢዎች የተረጋገጠ የምስክር ወረቀት ያላቸው በቅርብ ዓመታት ውስጥ የተመረቱ ዕቃዎችን የሰራተኞች የደንብ ልብስ፣ የጽ/ቤት አላቂ ዕቃዎች፣ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች ፣የተሽከርካሪ ጎማዎችን እና የሁለት እግር የሞተር ሳይክሎችን በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡ በዚሁ መሰረት ማናቸውም በንግድ ስራ ዘርፉ የተሰማሩ ህጋዊ የስራ ፈቃድ ያላቸው ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ እንዲወዳደሩ እንጋብዛለን::

1. ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ያላቸው የንግድ ፈቃዳቸውን ያሳደሱ የዘመኑን ግብር የከፈሉና ዋናና ቅጂ መረጃ አያይዘው ማቅረብ የሚችሉ፡፡
2. ተወዳዳሪዎች በአቅራቢዎች ዝርዝር ላይ የተመዘገቡበትን መረጃ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
3. ተወዳዳሪዎች ተጨማሪ እሴት ታክስ ( ቫት) ተመዝጋቢ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ መረጃ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
4. የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ በተመሰከረ ቼክ CPO 5000.00 ( አምስት ሺህ ብር ) በታሸገ ፖስታ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
5. በጨረታ የሚሳተፉ ተወዳዳሪዎች ከሙስናና ከብዝበዛ ድርጊት የጸዱ መሆን አለባቸው::
6. ጠቅላላ ተወዳዳሪዎች በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስትና የፌዴራል መንግስት የተደነገገውን የግዥ ሕግ የሚያከብሩ መሆን አለባቸው::
7. ተወዳዳሪዎች ጨረታውን ለማሰናከል ከሞከሩ ከጨረታው ውጭ ይሆናሉ ለወደፊትም በሠቃ ጨቆርሳ ወረዳ በሚካሄደው በመንግስት የግዥ ጨረታ አይሳተፉም :: ለጨረታ ማስከበሪያ ያስያዙት ገንዘብም አይመለስም ::
8. በኢትዮጵያ ደረጃ መዳቢዎች የተረጋገጠ ማቅረብ የሚችል::
9. ተወዳዳሪዎች የጨረታ ሰነድ ከተከፈተ በኋላ በሰነዱ ላይ ባቀረቡት የመወዳደሪያ ሀሳብ ላይ ለውጥ/ማሻሻያ ማድረግ ወይም ከጨረታ መውጣት አይችሉም ::
10. ተወዳዳሪዎች በጨረታው ላይ መግለጫ ወይም የማሻሻያ ጥያቄ ካላቸው በተመዘገቡ በአምስት ቀን ( 5) ውስጥ ማቅረብ ይችላሉ፡፡
11. ተወዳዳሪዎች ባቀረቡት መወዳደሪያ ሰነድ ላይ ስም ፣ ፊርማ ፣ የድርጅቱ ማህተም እና አድራሻ መጥቀስ አለባቸው ::
12. ተወዳዳሪዎች በጨረታው አካሄድ ቅሬታ ካላቸው ለሚመለከተው ክፍል ማቅረብ ይችላሉ፡፡
13. የጨረታውን ሰነድ በሠቃ ጨቆርሳ ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት ቁጥር 7 የማይመለስ 200 (ሁለት መቶ ብር ) በመክፈል መግዛት ይችላሉ፡፡
14. ይህ ጨረታ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ 15 (ለአስራ አምስት ) ተከታታይ የስራ ቀናት የሰነድ ሽያጭ ይከናወናል::
15. የጨረታ አሸናፊ ድርጅት ያሸነፈውን ዕቃ በራሱ ትራንስፖርት አጓጉዞ እስከ ጽ/ቤቱ ድረስ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡
16. መስሪያ ቤቱ እንደአስፈላጊነቱ 20% ጨምሮ ወይም ቀንሶ መግዛት ይችላል፡፡
17. የተሰረዘ፣ የተደለዘ የተፋፋቀ ወይም በግልፅ የማይነበብ የጨረታ ሰነድ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
18. ተጫራቾች የሚወዳደሩበትን ዋጋ መስሪያ ቤቱ ባዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ላይ በመሙላት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
19. የጨረታው ሰነድ አቅራቢ ድርጅቶች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በ16ኛው ቀን 3:00 ሰዓት ታሽጎ በቀኑ 4:00 ሰዓት ላይ ይከፈታል ::
20. ግዥ የሚፈጽመው አካል የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በጥቅል የመሠረዝ መብት አለው፡፡

**በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በጅማ ዞን የሠቃ**
**ጨቆርሳ ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት**

## ግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ
## ጨ.ቁጥር 01/2015

በቂርቆስ ክ/ከ/አስተዳደር ፐብሊክ ሰ/ሰ/ሀ/ል/ጽ/ቤት ፑል አስተዳደርና ፋይናንስ ግዥ አስተዳደር ቡድን ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ላይ ተጫራቾችን በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ዕቃ ወይም አገልግሎቱን መግዛት ወይም ማግኘት ይፈልጋል፡፡

| | የጨረታ ማስከበሪያ |
|---|---|
| 1. ሎት 1 የቢሮ አላቂ መገልገያ ዕቃዎች | ሲፒኦ ብር 5,000 |
| 2. ሎት 2 የተለያዩ የህንፃ መገጣጠሚያ ዕቃዎች | ሲፒኦ ብር 5,000 |
| 3. ሎት 3 ህትመት አገልግሎት | ሲፒኦ ብር 4,000 |
| 4. ሎት 4 ጫኝና አውራጅ አገልግሎት | ሲፒኦ ጥቃቅን |
| 5. ሎት 5 የፅዳት ዕቃዎች | ሲፒኦ ብር 9,000 |
| 6. ሎት 6 የጭነት መኪና አገልግሎት | ሲፒኦ ብር 5,000 |
| 7. ሎት 7 የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎቶች | ሲፒኦ ብር 10,000 |
| 8. ሎት 8 የመድረክ ማስዋብና ቅስቀሳ አገልግሎት | ሲፒኦ ብር 4,000 |
| 9. ሎት 9 ድንኳን ወንበርና ጠረጴዛ ኪራይ አገልግሎት | ሲፒኦ ብር 3,000 |
| 10. ሎት 10 ቋሚ ዕቃዎች እና የባህል አልባሳት | ሲፒኦ ብር 15,000 |

በመሆኑም ተጫራቾች፡-

1. የዘመኑን ግብር የከፈሉ በዘርፉ ሕጋዊ የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ እና የንግድ ምዝገባ ሰርተፊኬት፣ በአቅራቢነት የተመዘገቡ፣ የግብር መክፈያ መለያ ቁጥር /TIN No/ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰርተፊኬት ያላቸው፡፡
2. የጨረታው ሰነድ አቀራረብ 1 ቴክኒካል ሰነድ ኦሪጅናል 1 ቴክኒካል ሰነድ ኮፒ፣ 1 ፋይናንሻል ሰነድ ኦሪጅናል እና የፋይናንሻል ኮፒ ለየብቻ እንዲሁም 1 ሲ.ፒ.ኦ ወይም በባንክ የተረጋገጠ ለብቻ በታሸገ ኢንቨሎፕ መቅረብ አለበት፡፡
3. በጨረታው ላይ ጥቃቅን አነስተኛ ይበረታታሉ ሆኖም ግን የጨረታ ሰነዱን በነፃ ማግኘት የሚችሉት ካቋቋማቸው አካል ተገቢውን እና የተሟላ ማስረጃ ሲያቀርቡ ብቻ ነው፡፡
4. ወቅታዊ የሆነ የመልካም ሥራ አፈጻጸም የሥራ ልምድ ማቅረብ የሚችል፡፡
5. የጨረታ ሰነዱን እስጢፋኖስ አካባቢ በሚገኘው የቂርቆስ ክፍለ ከተማ አስተዳደር አዲሱ ህንፃ 6 ፎቅ የፐብሊክ ሰ/ሰ/ሀ/ል/ጽ/ቤት የመንግስት ግዥ አስተዳደር ቡድን ቢሮ ቁጥር 115 በመቅረብ ይህ ማስታወቂያ በ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 ተከታታይ የሥራ ቀናት የማይመለስ ብር 100.00 በመክፈል ሰነዱን መግዛት ይችላሉ፡፡
6.ጨረታው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንድ ቀን ብሎ በመቁጠር ለ10 የሥራ ቀናት የሚቆይ ሲሆን የሚከፈተው ደግሞ 11ኛው ቀን ላይ ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት የጨረታ ሳጥኑ የሚዘጋ ሲሆን በተመሳሳይ ቀን ከጠዋቱ 4፡30 ላይ ጨረታው ይከፈታል፡፡
7. ተጫራቾች በጨረታ ሰነዱ ላይ እንደ ማሳሰቢያ የተጠቀሱትን ማስረጃዎች ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
8. አሸናፊ ድርጅት አሸናፊነቱ ከተገለፀለት ከ7 ተከታታይ የሥራ ቀናት በኋላ በግንባር ቀርቦ አሸናፊ የሆነበትን ጠቅላላ ዋጋ 10 በመቶ የውል ማስከበሪያ በማስያዝ በ8 ቀናት ውስጥ ውል መያዝ አለበት ::
9. መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

**አድራሻ፡-** እስጢፋኖስ ከሚገኘው ከማሪዎት ሆቴል ፊትለፊት የቂርቆስ ክ/ከ/አስ/ አዲሱ ህንፃ 6ኛ ፎቅ
ስልክ 0115-58-28-71

**ማሳሰቢያ፡-** የመኪና ምርታቸው እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከ 2007 G.C ጀምሮ የሆነ መሆን አለበት፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር**
**የቂርቆስ ክ/ከተማ ፐብሊክ ሰ/ሰ/ሀ/ል/ጽ/ቤት**

## ግልፅ የጨረታ ማስታወቂያ

በኦሮሚያ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን የደ/ሊባኖስ ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት በ2015 የበጀት ዓመት ለወረዳው አገልግሎት የሚውል የሰራተኞች የደንብ ልብስ፣ አላቂ የጽህፈት መሳሪያዎች፣ የጽዳት ዕቃዎች፣ ኤሌክትሮኒክስና ፈርኒቸሮችን በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

ስለዚህ በጨረታው ለመሳተፍ የምትፈልጉ ተጫራቾች፤

የቫት ተመዝጋቢ የሆኑ፣ የዘመኑ የታደሰ የንግድ ፈቃድ ያላቸው፣ የዘመኑን የመንግስት ግብር የከፈሉ፣ የገንዘብ ሚኒስቴር ባወጣው የዕቃ አቅራቢዎች ዝርዝር የተዘገቡበትን ማስረጃ የሚያቀርቡ እና የቫት ተመዝጋቢ የሆኑ መሆን አለባቸው፡፡

ተጫራቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለተከታታይ 15 የሥራ ቀናት የጨረታ ሰነዱን ዘወትር በሥራ ሰዓት የማይመለስ ብር 100 /አንድ መቶ ብር/ በመክፈል ደብረ ሊባኖስ ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት ቢሮ ቁጥር 1 መግዛት ይችላሉ፡፡

ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ ብር 5,000/ አምሥት ሺህ ብር/ በባንክ በተሰከረለት ቼክ /CPO/ብቻ ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

ጨረታውን ያሸነፈ ተጫራች ባሸነፈባቸው የዕቃ ዝርዝር መሰረት ከመ/ቤቱ ጋር የውል ስምምነት መፈራረም ይኖርበታል፡፡

ተጫራቾች ዕቃዎቹን ከነ ትራንስፖርት ወጭያቸው የሚሸጡበትን ዋጋና አይነት በመለየት በተዘጋጀው ዝርዝር ሰነድ ላይ ሞልተው በታሸገ ኤንቨሎፕ ኦሪጅናል እና ኮፒ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ እስከ 15ቀን ዘወትር በሥራ ሰዓት 2፡30-11፡30 ድረስ በሥራ ቀናት ውስጥ ለዚህ ሲባል በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡

ጨረታው በ16ኛው ቀን በ4፡00 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ተዘግቶ በዚሁ ቀን በ5፡00 ሰዓት ይከፈታል፤ 16ኛው ቀን ቅዳሜ እሁድ ወይም የበዓል ቀን ከሆነ በሚቀጥለው የሥራ ቀን ይካሄዳል፡፡

ተጫራቾች በሚፈልጉትና ማቅረብ በሚችሉበት ዕቃዎች ላይ ብቻ መወዳደር ይችላሉ፡፡ ሆኖም ለአንድ ዓይነት ዕቃ ከተጠየቀው ብዛት አሳንሶ ማቅረብ አይቻልም፡፡

ተጫራቾች በጨረታው ተወዳድረው ያሸነፉባቸውን ዕቃዎች ደ/ሊባኖስ ወረዳ ገ/ጽ/ቤት ዕቃ ግምጃ ቤት የማጓጓዣ የማስጫኛና የማውረጃ ወጪ መቻል ይኖርባቸዋል፡፡

መ/ቤቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ተጫራቾች ያሸነፉበትን የዕቃ አይነት ወይም ናሙና ማቅረብ አለባቸው፡፡

ማብራሪያ በስልክ ቁጥር 0111-33-05-44 ዘወትር በሥራ ሰዓት በመደወል ወይም ደ/ሊባኖስ ወረዳ ገ/ጽ/ቤት ዕቃ ግዥ ክፍል በግንባር ቀርበው መረዳት ይችላሉ፡፡

አድራሻ፡- በሰሜን ሸዋ ዞን የደ/ሊባኖስ ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት ከአ.አ በስተ ሰሜን 89 ኪ.ሜ ሸረሮ

**በኦሮሚያ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን የደ/ሊባኖስ**
**ወረዳ ገንዘብ ጽ/ቤት**